## ዜናዎች

# አንዳርጋቸው ጽጌና ኢሳያስ አፈወርቂ አስመራ ውስጥ ተወያዩ

## ዶ/ር ብርሀኑም ኤርትራን ለመጎብኘት በዝግጅት ላይ ናቸው

### ንቅናቄው ከኢትዮጵያ ጠላት ጋር አብሮ ሲሰራ አይገባም ሲሉ አንዳንዶች ተቃውሞ አሰሙ

*ሪፖርታዥ*

የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ መስራችና ዋና ጸሐፊ የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ኤርትራ መግባታቸውን ለንቅናቄው ቅርብ የሆኑ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ::

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ለንቅናቄው የሚሆን ማዕከላዊ ጽ/ቤት አስመራ ውስጥ ለመክፈት ባለፈው ቅዳሜ አስመራ መግባታቸውንና ከፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ እና ከሌሎች የአገሪቱ ባለስልጣናት ጋር እንዲሁም መሰረታቸውን ኤርትራ ካደረጉ ተቃዋሚዎች ጋር ውይይት በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል::

ዶ/ር ብርሀኑም ከሳምንታት በኋላ አስመራን ለመጎብኘት በዝግጅት ላይ እንደሚገኙ የገለጹት ምንጮቻችን ዶክተሩ በአስመራ ቆይታቸው ከአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ እና ከሌሎች የኤርትራ ባለስልጣናትና ጀነራሎች ጋር በንቅናቄው አላማና የትግል ስትራተጂ ዙሪያ እንደሚመክሩ ጨምረው ገልጸውልናል:: ይህ ዜና ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያን ሪቪው ድረ ገጽ ይፋ መደረጉን ተከትሎ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በተለያዩ ድረ ገጾች በዶ/ር ብርሀኑ ላይ ድጋፍም ተቃውሞም እየሰነዘሩ ይገኛሉ::

አዲስ አበባ ውስጥ አውራምባ ታይምስ በዚሁ ጉዳይ ያነጋገራቸው አስተያየት ሰጪዎችም ሁኔታውን በጥርጣሬ ተመልክተውታል:: አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ይህንኑ አስመልክተው ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት «የሻዕቢያ ጥላቻ በኢህአዴግ መሪዎች ላይ ብቻ ነው ብሎ መደምደም የዋህነት ነው» ብለዋል መምህሩ አያይዘውም «አሁን በኤርትራ ስልጣን ይዞ የሚገኘው አመራር በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ጥላቻ ያለው ነው ካሉ በኋላ ከእንዲህ አይነት የጎረቤት ጠላት ጋር መስራት መዘዝ አለው» በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል:: ያነጋገርናቸው ሌላ አስተያየት ሰጪ ግን በዚህ አይስማሙም ንቅናቄው ከአቶ ኢሳያስ ጋር መስራት የፈለገበት ምክንያት-ሻዕቢያ ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ ስለሆነ፤ አሊያም ደግሞ በአገራችን ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ፍላጎት

አለው ብሎ ስለሚያምን ሳይሆን ንቅናቄው ከሚከተለው ሁሉን አቀፍ የትግል ስልት አንጻር ለትግሉ ብቸኛዋ የስትራተጂ ቦታ ኤርትራ በመሆኗና ምርጫም ስለሌለው ነው ብለዋል፡፡

በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ትልቅ የመነጋገሪያ አጀንዳ የሆነው ይህ ዜና ኢህአዴግን አጥብቀው በሚያወግዙ ድረገጾችና ቡድኖች ዘንድም በአወንታዊና አሉታዊ ጎኑ እየተንጸባረቀ ይገናል፡፡ አሌክስ ብርሀኑ የተባሉ ጸሀፊ በ *nazret.com* ድረ ገጽ The Ginbot Guys Did It As Predicted! (ግንቦት ሰባቶች ቀደም ሲል የተገመተውን አደረጉት!) በሚል ርዕስ ባሰፈሩት ሀተታ እርምጃው «የኢትዮጵያን ህዝብ ሞራል የማይመጥን» ብለውታል፡፡ ከወ/ሪት ብርቱካን ዳግም መታሰር ጋር በተያያዘ ኢህአዴግን የሚተቹ ጽሁፎችን በተለያዩ ድረ ገጾች ላይ በመጻፍ የሚታወቁት የቺካጎው ግርማ ካሳ በበኩላቸው የአስመራ ትዝታዬ በሚል ርዕስ በጻፉት መጣጥፍ «በኤርትራ ያሉ ወገኖቻችን በላያቸው ላይ የግፍ ቀንበር ተጭኖባቸው አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ለተቀረው ኢትዮጵያዊ መፍትሄ ይሆናሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡» ይላሉ አቶ ግርማ፡፡ ይሁንና የግንቦት 7ን እርምጃ በመደገፍ ከንቅናቄው ጎን እንደሚቆሙ ያረጋገጡት ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ቁጥር እጅግ በርካታ ነው፡፡

አንድ አዲስ አበባ ውስጥ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩና የዶ/ር ብርሀኑን እንቅስቃሴ እንደሚደግፉ የሚገልጹት አስተያየት ሰጪ ደግሞ «እነ ዶ/ር ብርሀኑ እንዲህ አይነት ስህተት ውስጥ ይገባሉ ብዬ አላምንም፤ወደ ኤርትራ የሚደረገው ሩጫ «የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው» በሚል ጊዜያዊ እልህ ብቻ የተቃኘ መሆን የለበትም፤ ሻዕቢያ የሁላችንም ጠላት ነው፡፡ ይሁን ቢባል እንኳን ትግሉ ሲሳካ ሻዕቢያ የሚደግፈን ለጽድቅ ብሎ አይደለምና ከኛ ወፍራም ካሳ ይፈልጋል የምንከፍለው ካሳ ደግሞ የዛኑ ያህል ከባድ ስለሚሆን ከአመታት በፊት ኢህአዴግ የሰራውን ስህተት መድገም ነው የሚሆነው፡፡ ሻዕቢያ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት ነውና እነ ዶ/ር ብርሀኑ ደጋግመው ሊያስቡበት ይገባል» ብለዋል፡፡

በዚሁ ዙሪያ የኢትዮጵያ መንግስት አቋም ምን እንደሆነ ለማወቅ የአውራምባ ታይምስ ዝግጅት ክፍል ያደረገው ሙከራ ለጊዜው ባይሳካም አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች የጸረ-ሽብርተኝነት ህጉ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቆ በአፋጣኝ ወደ ፓርላማ እንዲላክ የተደረገበት ምስጢር ንቅናቄው በአገር ውስጥ በሚያደርገው እንቅስቃሴ የደጋፊዎቹን አንገት ለማስደፋት ነው ይላሉ፡፡ በአዲሱ የጸረ ሽብር ረቂቅ አዋጅ መሰረት መንግስት አሸባሪ ብሎ ለፈረጃቸው ወገኖች ሽፋን የሚሰጥ ሚዲያ ከእድሜልክ እስከሞት በሚያስቀጣ ወንጀል ይጠየቃል ይላል፡፡

# የጸረ-ሽብርተኝነት ረቂቅ አዋጅ ወደ ፓርላማው ተመራ

ባለፈው ሳምንት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀረ-ሽብርተኝነት ረቂቅ አዋጅን አጽድቆ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መላኩን የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት በትናትንናው ዕለት በሰጠው ሳምንታዊ መግለጫ አስታውቋል፡፡ በመግለጫው ላይ «ኢትዮጵያ በአል-ኢትሀድ፣

በኦነግ፣ በኦብነግ እና በመሳሰሉ ቡድኖች ሳቢያ የሽብር ሰለባ ሆና ቆይታለች» ያሉት የመንግስት ኮሙኒካሽን ጉዳዮች ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴዔታ አቶ ኤርሚያስ ለገሠ መንግስት ለረቂቅ አዋጁ መጽደቅ ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው ያላቸውንም ዘርዝረዋል፡፡ ከዋና ዋና ምክንያቶቹ መካከልም ሀገሪቱ የሽብር ሰለባ መሆኗ እና በርካታ ውድመቶች መድረሳቸው የመጀመሪያው ሲሆን በሀገሪቱ ራሱን የቻለ የሽብርተኝነት የወንጀል ሕግ አለመኖሩ፣ የሕግ አስከባሪ አካላት ሽብርተኝነትን በብቃት እንዲከላከሉ ሕጋዊ ሥልጣን ለመስጠት እና ከሌሎች የዓለም ሀገራት ጋር በጋራ ለመስራት እንዲያስችል ረቂቅ አዋጁ መዘጋጀቱ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም የፀረ-ሽብርተኝነት ረቂቅ አዋጁ ከአስራ ሁለት ያላነሱ የዓለም አቀፍ የሽብርተኝነት ስምምነቶችን፣ የአፍሪካ የሽብርተኝነት ፕሮቶኮሎችን፣ እንዲሁም የተለያዩ ሀገራት ሕጎችን ግብዓት ያደረገ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀው ረቂቅ አዋጅ በይዘቱ የሽብርተኝነት ድርጊትን ዘርዝሮ ያስቀመጠ ሲሆን ድርጊቱን መፈፀም ወይም ማስፈፀም፣ ለመፈፀም ማቀድ ወይ መዘጋጀት፣ እንዲሁም ድርጊቱን መደገፍ ወይም ማበረታታት ወንጀል መሆናቸውን አካትቷል፡፡ ከዚህም በላይ ድረጊቱን በጽሁፍም ሆነ በተለያዩ የሚዲያ ዘርፎች ማስተዋወቅ፣ መቀስቀስ እና ማወደስ ከወንጀል እንደሚቆጠር በረቂቅ አዋጁ መካተቱን አስመልክቶ ከፕሬስ ጋር በተያያዘ ምናልባትም በቀና ልቦና የተሰሩ የዘገባ ስህተቶች እንደ ወንጀል ስለመቆጠራቸው ከጋዜጠኞች ለተነሱ ጥያቄዎች የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስቴር ዴዔታ አቶ ሽመልስ ከማል ( አቶ ሽመልስ ቀደም ሲል የቅንጅት አመራሮችን ጉዳይ አቃቤ ህግ ሆነው ሲከታተሉ የነበሩ መሆናቸውን ልብ ይሏል) ሲመልሱ «ሽብርተኛው ለመናገር መብት የሌለውን ነገር ጋዜጠኛው አትሞ የማውጣት ልዩ መብት አለው ማለት አይደለም፡፡» ብለዋል፡፡ ሆኖም በረቂት አዋጁ የተካተተው ሕግ የሽብርተኛ ድርጊቶቹን ለማስተጋባት እና ለማወደስ ሆን ተብለው የተሰሩ ዘገባዎችን እንደሚከለክል እንጂ በቀና ልቦና የተሰሩ ስህተቶችን አለመሆኑንም አቶ ሽመልስ አስረድተዋል፡፡ ከዚህም በላይ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግም ቢሆን ሌሎች የወንጀል ድርጊቶችንም በአደባባይ ማወደስ እንደማይቻል ማስቀመጡን ጨምረው ጠቁመዋል፡፡ ሕዝቡን ለማወክ ሀሰተኛ መረጃዎችን ማስተላለፍ፣ «እንዲህ ዓይነት ቦታ ላይ ሽብር ተፈጽሟል፣ ሊፈፀም ነው» የሚሉ የእውነት መሰረት የሌላቸው መረጃዎች እንዳይዘገቡ በረቂቅ አዋጁ መደንገጉም ተገልጿል፡፡

ከሽብርተኝነት ጋር በተያያዘ የሚከናወኑ ምርመራዎችንም በተመለከተ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት የመንግስት አካል ከፍርድ ቤት ፍቃድ በመውሰድ ስልክ፣ ኢንተርኔት፣ ደብዳቤና የመሳሰሉትን መገናኛዎች መጥለፍ እንደሚችል እና ድንገተኛ ፍተሻዎች የሚደረጉበትንም ሁኔታ የፀደቀው ረቂቅ አዋጅ ይፈቅዳል፡፡ ማንኛውም አከራይ በ24 ሰዓት ውስጥ የተከራዩን ማንነት እና ያለበትን ሁኔታ ለፖሊስ የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት፤ መንግስት በሽብርተኝነት የተጠረጠረን ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መያዝ እንደሚችል፤ እንዲሁም ተጠርጣሪውን በ48 ሰዓት ውስጥ አቅርቦ ፖሊስ በአጠቃላይ ከአራት ወር የማይበልጥ የ28 ቀን የጊዜ ቀጠሮ መጠየቅ እንደሚችል ረቂቅ አዋጁ አስፍሯል፡፡ በአዋጁ መሰረትም የሰሚ ሰሚ (የአሉ አሉ) ማስረጃ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

በሽብር የተጠረጠረው ሰው ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊታሰር/ሊያዝ መቻሉን በተመለከተ አቶ ሽመልስ «ሕገ መንግስቱ በ48 ሰዓት ወደ ፍርድ ቤት ይቅረብ እንጂ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አይታሰር አይልም።» ሲሉ የ28 ቀን የጊዜ ቀጠሮን በተመለከተ ደግሞ አቶ ኤርሚያስ ረቂቅ አዋጁ ታሳቢ ካደረጋቸው ጉዳዩች መካከል «የሽብርተኝነት ጉዳይ ውስብስብ የወንጀል ባህሪ» ስላለው እንደሆነና ተጠርጣሪው ሳይታሰር ምርመራ ይደረግ ቢባል ሊያመልጥ እንደሚችል ገልፀዋል። የሰሚ ሰሚ ማስረጃ በፍርድ ቤት ተቀባይነት እንዲያገኝ መሆኑንም አስመልክቶ ከጋዜጠኞች ለተነሳ ጥያቄ አቶ ሽመልስ ሲያብራሩ ከዚህ ቀደምም ቢሆን ሀገሪቱ በምትከተለው የሕግ ሥርዓት አኳያ (continental law) የሰሚ ሰሚ ማስረጃዎችን መቀበልን «የሚከለክል ድንጋጌ የለም» ብለዋል።

ባለፈው ሳምንት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተመራው የፀረ-ሽብርተኝነት ረቂቅ አዋጅ አንድን የሽብር አካል ሽብርተኛ ነው ወይም አይደለም ብሎ የመሰየም ወይም የመሻር ሥልጣን የሰጠው ረቂቁን አዋጅ አድርጐ እንዲያፀድቅ ለተላለፈለት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደሆነም ታውቋል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ይህንን ሥልጣኑን ሲያከናውን የመሰየሚያ ነጥቦች እንደተቀመጡለትና ነጥቦቹም ይህ አካል የሽብር ዓላማ ካለው፣ የፈፀመ ወይ ያስፈፀመ ከሆነ፣ ለመፈፀም የተዘጋጀ ከሆነ፣ እንዲሁም የሽብር ተግባሩን ከደገፈና ካበረታታ በሽብርተኝነት ሊሰይመው እንደሚችል ተገልጿል። የመሰየም ሥልጣኑ ለሕዝብ ተወካዮች እንዴት ሊሰጠው ቻለ በሚለው ላይ አቶ ኤርሚያስ «የሕዝብ ውክልና ያለው አካል ምዘናውን እንዲወስድ» ነው ካሉ በኋላ በሌሎች ሀገራት ተሞክሮ፣ ለምሳሌ በእንግሊዝ፣ በሕንድ እና በካናዳ የመሰየም ሥልጣኑ የአስፈፃሚው አካል እንደሆነ አብራርተዋል።

ከሽብርተኝነት ተግባር ጋር በተያያዘ የተገኘ ንብረትን በተመለከተም ንብረቱ ተወርሶ የሽብር ተጎጂዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበት የሽብርተኝነት ተጎጂዎች ፈንድ እንደሚቋቋም ለማወቅ ተችልዋል።

# የክቡር ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ የ40 ቀን መታሰበያ ስነ ስርዓት ትናንት ተከናውኗል።

የአንፀባራቂው ኮኮብ ጥላሁን ገሠሠ አስክሬን ሚያዚያ 15 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 10:47 ላይ በክብር ካረፈበት በስላሴ ቤ/ክ ትላንት የፀሎት ስነ ስርዓት ተፈጽሞለታል። ከአንድ ሺህ በላይ ለሚገመቱ ነዳያንም የምሳ ግብዣ ተደርጓል። በእለተ ፋሲካ ህይወቱ አልፎ ሚያዝያ 15 ቀን በመቶ ሺህዎች በሚቆጠሩ አድናቂዎቹና ቤተሰቦቹ በተገኙበት የቀብሩ ስነ ስርዓት የተፈፀመው የአርቲስት ጥላሁን ገሠሠ የአሟሟት ሁኔታ አነጋጋሪ እየሆነ መጥቷል።

የጤና ጥበቃ ሚ/ር የአርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ህልፈተ ህይወት በሕክምና ባለሙያዎች በተፈፀመ ስህተት ይሆን? በሚል በሆስፒታሎች ላይ ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ያስተላለፈ ሲሆን፤ ይኸ ዜና እስከተጠናቀረበት ሰዓት ስለምርመራው ውጤት የተገለፀ ነገር አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል።

የንጉሥ ጥላሁን የ40 ቀን መታሰቢያ ትናንት በፀሎት ከታሰበ በኋላ ባለቤቱ ወ/ሮ ሮማን በዙ «ሐዘኔን እንድረሳ ነው ያደረገኝ» በማለት ለኢትዮጵያ ህዝብ የምስጋና መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ወ/ሮ ሮማን በዙ ትናንት ባስተላለፉት መልዕክት «ጥላሁን በሚወደውና በሚያፈቅረው ህዝብ ታጅቦ የቀብር ስነ ስርዐቱ ተፈጽሟል፤ ሕይወቱ ካለፈበት ግዜ ጀምሮ የሐዘናችን ተካፋይ በመሆን ላጽናኑን፤ ከጐናችን ሳይለዩ ድጋፋቸውን በተለያየ መንገድ ለገለፁልን ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ» ብለዋል። «ጥላሁን ህይወቱ ቢያልፍም በሚወደው ህዝብ ልብ ውስጥ ስሙ ለዘላለሙ ታትሞ እንደሚኖር አረጋግጫለሁ። ይኼም ሐዘኔን እንድረሳ አድርጎኛል» በማለት ገልፀዋል።

የድምፃውያኑ ንጉሰ-ነገስት ጥላሁን ገሰሰ በህይወቱ ዘመኑ አስገራሚ እውነታዎች አስተናግዶ ያለፈ መሆኑን የደረሰን መረጃ አመላክቷል።

ጥላሁን በአንድ ወቅት በሰጠው መግለጫ ሐገር ፍቅር ተፀንሼ ክቡር ዘበኛ ነው የተወለድኩት በማለት፤ በድምጻዊነቱ ከየት ተነስቶ ለታላቅ ክብርና ዝና እንደበቃ ገልጿል። «በዘፋኝነቴ አምኜበትና ተደስቼበት፣ ተዋግቼበትና አዋግቼበት ከዚህ ደረጃ ላይ በመድረሴ በጣም እኮራለሁ። ከዚህ በኋላ ከዘፈን የሚለየኝ የህይወቴ ፍፃሜ ብቻ ነው» ያለው ጥላሁን፣ በእለተ ፋሲካ ህይወቱ ካለፈ በኋላ ትናንት 40 ቀኑ ታስቦ ማለፉ ብዙዎችን አስደምሟል።

## መጣጥፎች

# አፈር ስሆን...!
# «ሰኔ እና ሰኞ» እንዳይገጥሙ መላ ፈልጉ!

አቤ ቶኪቻው
abeto2007@yahoo.com

ወዳጄ እንደምን ሰነበቱ? ዘንድሮ ሰኔ እና ሰኞ ሊገጥሙ እየተንደረደሩ ነው። ይህ ደግሞ በሀገራችን ባህል መሰረት የደግ ነገር ምልክት አይደለም። እንደውም አንዳንዶች «ሰኔና ሰኞ የገጠሙ ዕለት በተለይ ለመንግስት ያሰጋል» እያሉ ሲያስፈራሩን ጊዜ፤ ለመንግስታችን በጎ አሳቢ የሆንን ሁላ ተሰብስበን «ሰኔና ሰኞ» እንዳይገጥሙ በፀሎት እየተጋን (ኢቴቪ ለህዳሴው እውን መሆን እንደሚተጋውእ) እንገኛለን። ከዚህ ጋር በተያያዘ ከወደ ማብቂያችን ጥቂት እንጨምራለን ከዛ በፊት ደግ ደጉን:-

ባለፈው ሳምንት ስለ ግንቦት ሃያ በጥቂቱ መነካካታችን ይታወሳል። ቢሆንም ግንቦት 20ን የሚያክል ግዙፍ በዓል ገና ለገና ባለፈው ሳምንት አውግተናል ብለን ዛሬ ሳናወራ ብንዘለው የድሉን ግዝፈት ማጣጣልና በዓሉንም ማኮሰስ ይሆንብናል። እና ዛሬም አንዳንድ ጉዳዮችን ስለ

ግንቦት ሃያ ላወጋዎ ነው፡፡ ይህ የሆነው ለበዓሉ ያለኝን ክብር ለመግለፅ እንደሆነ ይታወቅልኝ ዘንድ አደራ እላለሁኝ፡፡

ታድያ «እንኳን ለብረሃነ ግንቦት ሃያው በሰላም አደረሳችሁ!!» በማለት ብንጀምር ምን ይለናል!? ግንቦት ሃያ እኮ ብርሃን ነው! (ምነው ሳቅዎ መጣ?!) በእርግጥ አንዳንድ ፅንፈኛ ወዳጆቼን በስልክ እና በአካል «እንኳን ለብረሃነ ግንቦት ሃያው በሰላም አደረሳችሁ!!» ባልኳቸው ወቅት «በሻማ ብርሃን እያከበርነው የምን ብርሃነ-ግንቦት ሃያ ነው?» ሲሉ ጠይቀውኛል፡፡ ወይ ጉድ ይሔ መብራት ለስንቱ ትችት ዳረገን ጎበዝ? አንድ የመብራት እጥረት አጋጠመና የግቦት ሃያን ድል ማጣጣል ተገቢ ነው? በርግጥ ያጋጠመን ችግር የመብራት እጥረት ብቻ ሳይሆን የውጪ ምንዛሪ እጦት፣ የዋጋ ግሽበት፣ የመጠጥ ውሃ ችግር፣ የመልካም አስተዳደር ችግር ሌላም ችግር አሁንም ሌላ ችግር አጋጥሞን ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ለበዓሉ ድምቀት ስንል ምናለ ክፉ ክፉውን ትተን ደግ ደጉን ብቻ እደግመዋለሁ ደግደጉን ብቻ ብናይ!?

ስለ በዓሉ ድምቀት አንስተን የመጣ ቢመጣ የማናልፋትን አንድ ጨዋታ በቅንፍ እናውራ እና እንመለሳለን (በታክሲ ላይ ተሳፍረናል ዕለቱ ግንቦት ሃያ ነው፡፡ የታክሲው ወያላ የሞላው ታክሲ ላይ ሰዎችን እየደራረበ ይጭናል፡፡ ተሳፋሪውን ለማግባባት ይሁን፤ ከልቡ ይሁን በማይለይ ድምፅ «እባካችሁ ለበዓሉ ደምቀት ጠጋ ጠጋ በሉ» ሲል እኔና በርካቶች ለበዓሉ መልካም አስተያየት ያለን ግለሰቦች ለበዓሉ ድምቀትስ ከሆነ እንጠጋጋለን!» እያልን ስንጠጋጋ በበዓሉ ድምቀት አይናቸው ከሚቀላ መካከል የመሰለኝ አንዱ ሰው «አልጠጋም» አለ፡፡ በዚህ ጊዜ እኔ ተበሳጭቼ «ምናለ ወንድሜ ለበዓሉ ድምቀት አስተዋፅኦ ብታደርግ...? ይሔ ድል እኮ...» ብዬ ማብራሪ ገና ስጀምር «በሞቴ ስለ ድሉ ማብራሪያ እንዳትነግረኝ ገብቶኛል! ገብቶኛል! ነገር ግን በዓሉ የነፃነት እንጂ የጭንቅ በዓል ስላልሆነ አልጠጋም» አለኝ፡፡ እውነቱን ነው፡፡ አሁን ወያላውን ነው መምከር! ስል በማሰብ ዝም አልኩኝ፡፡) እናም ለበዓሉ ድምቀት ስንል ያሉትን ችግሮች እንደሌሉ ቆጥረን እንደ ኢቲቪ መልካም መልካሙን ብቻ ብናወራ ደግ አይደለም? ለምሳሌ በግንቦት ሃያ ማግስት የተመረቀው የጎተራው ቀለበት መንገድ ወይም «የብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መንገድ» ግንባታን መጠናቀቅ እያወጋን መደሰት ደግ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ይህ አዲሱ ግንባታ መንገድ ሳይሆን «ማሳለጫ» ነው የሚባለው፡፡ ተስተካክሎ ሲነበብ «የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ማሳለጫ» ይሆናል ማለት ነው፡፡

እውነቱን ለመናገር ይህ በግንቦት ሃያ ድል ማግስት የተመረቀው «የብሔር ብሔሮች እና ህዝቦች ማሳለጫ» ውብ ነው፡፡ በርግጥ ወደ «ማሳለጫው» ሲሔዱ በደብረ ዘይት መንገድ ያለው ኮረኮንች መንገድ «አናስገባም ሰርገኛ» የሚል ይመስል በጣም ያስቸግራል፡፡ እውነት ይሔ መንገድ ግን ምነው ቆሞ የቀረ ይመስላልሳ? በዛ በኩል በርካታ ጊዜ የማለፍ የማግደም ዕድል አጋጥሞኛል ነገር ግን አንድም ቀን ሰዎቹን በስራ ላይ አይቻቸው አላውቅም፡፡ ሁልጊዜ የሻይ ሰዓት ላይ ናቸው እንዴ? አቦ ቶሎ ቶሎ ስሩልንና «በብሔር ብሔረሰብ እና ህዝቦች ማሳለጫ» ላይ እንደልባችን እንሳለጥ እንጂ!

በነገራችን ላይ ግንቦት ሃያን የምናከበርው በኢኮኖሚ እድገት ብቻ ሳይሆን በቋንቋ እድገትም ታጅበን መሆኑን አንዳንድ የአማርኛ መምህሮች እየገለፁ ይገኛሉ፡፡ መምህራኖቹ አያይዘውም «ተኮር፣መር፣ህዳሴ፣ማሳለጫ እና የመሳሰሉት ቃላት የግንቦት ሃያ ፍሬ ናቸው፡፡ በመሆኑም ለቃላት እድገት አለኝታ የሆነው ኢህሃዴግ መቶ አመት ይንገስልን!! እነሆ ቃላትንም ይመግበን

እንጠግብማለን!» ብለዋል። እና ለበዓሉ ድምቀት ስንል የኢኮኖሚ፣ የመንገድ እና የቃላት እድገታችንን እያጣጣምን ብንደሰት ምናለበት!?

ስለ አማርኛ ካነሳን አይቀር ለግንቦት ሃያ ድል መግለጫ ከተሰቀሉት መፈክሮች ሁሉ በርካታ ቦታ በመሰቀል ሪከርድ የያዘው «ግንቦት ሃያ ለዴሞክራሲ መሰረት!!» የሚለው ሃረግ ነው። ይህ በጅምር የቀረ ሃረግ የአማርኛ ሊቅ ያልሆኑትን ሁሉ ሲያነጋግር ሰንብቷል። አንዳንዶች «ፈካሪው» ወይም መፈክር ፀሃፊው እየፃፈ ሳለ ጨርቅ አነሰው እና «ግንቦት ሃያ የዴሞክራሲ መሰረት...» ብሎ፤ ነውም ሳይል፣ አይደለምም ሳይል፣ ሊሆን ይችላልም ሳይል በጅምር ትቶታል ሲሉ። ሌሎች ደግሞ «የለም ይህ መፈክር ፀሃፊ ምንም የጨርቅ እጥረት አላጋጠመውም ምንም እንኳ የታዘዘው «ግንቦት ሃያ የዴሞክራሲ መሰረት ነው!» ብለህ ፃፍ» ተብሎ ቢሆንም እርሱ ግን «ለምን ይዋሻል?» በሚል ህዝቡ ይፍረድ ብሎ ጅምሩን ሃረግ ፃፈው ይላሉ። የሆኖ ሆኖ እኛ ከግንቦት ሃያ በረከት የተቋደስነው ሰዎች «ግንቦት ሃያ የዴሞክራሲ መሰረት ነው!!» እያልን አሟልተን ስናነብ ሌሎችም እንደየቁስላቸው መጠን፤ «ሊሆን አይችልም፣መሆን ነበረበት፣ይሆናል ብለን ነበር፣ካልሆነ በቃችሁ!...» ወዘተ እያሉ ያሻቸውን ሲሞሉ አይቼ አንዱ ወዳጄን «እንዲህ ነገር ማጣመም ተገቢ ነው?» ብዬ ብጠይቀው። «ድሮውኑ አስተካክላችሁ መፃፍ ነበራችሁ» አለኝ። አሃ... ለካስ ሰውዬው ከነ አጅሬ ወገን ነውና ለምን ደስ ይበለው ብዬ «ምንም አላቹ ምንም ይኸው አስራ ስምንተኛ ሻማችንን ለኮስን ምን ትሆኑ?» አልኩት እንቁልጭልጭ በሚል ስሜት። ወዳጄ ትንሽ ተከዝ ብሎ «በቴሌቪዥን አስራ ስምንት ቁጥር ሻማ ስትለኩሱ አይቻለሁኝ።» አለኝ። «ገና ምን አይተህ ሰላሳ ስምንት ቁጥርን እንለኩሳለን!» አልኩት። ምቀኝነት ያስተከዘው ወዳጄ «አስራ ስምንት አመት እንደሻማዋ ያቃጠላችሁን አንሶ ሰላሳ ስምንት አመት? ማቃጠልም እኮ ይደክማል አረ ትንሽ አረፍ እያላችሁ ይሻላችኋል!» አለኛ ። ወዳጄ ይህ አይነቱን ፅንፈኛ ይተዉት እና እልቅስ ከአስራ ስምንት አመት ጋር በተያያዘ በሆነ ጋዜጣ ላይ ያነበብኩት «ኢሃዴግ እስከዛሬ ቢያጠፋም ለአቅመ አዳም አልደረሰም ነበርና አያስከስሰውም አሁን ግን የአስራ ስምነት አመት ጎረምሳ ነው» የሚል ሃሳብ የያዘው ፅሁፍ ተመችቶኛል። እውነትም እንዲህ ልብ ላለው ሰው እስከዛሬ ስናውቅ በድፍረት ሳናውቅ በስህተት የሰራነውን በሙሉ ይቅር መባል አለብን። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከወዳጆቼ ጋር ስናወጋ አንዱ «ለካስ ደርግ በልጅነቱ ኖሯልና የተቀጠፈው!» ሲል ሌላውም ሰሞኑን «የደርግ ባለስልጣናት በይቅርታ ሊፈቱ ነው» የሚለው ዜና አጣቅሶ «ለዚህ እኮ ነው ይቅርታው ይፀድቃል የተባለው።» አለን። ለነገሩ ደርግ እንኳ ገና ጡጦ ሳይጥል የሚሰራውን አሳጥቶት ነበር። ነገር ግን ይሔ ይቅርታ ቢፀድቅ  እውነቱን ለመናገር እንደ ፅድቅ ይቆጠራል። (ሁሉም ነገር እኮ ነግ በኔ ነው።)

ለግንቦት ሃያ በዓል ድምቀት እጅግ ከሚጨነቁት አንዱ የሆነው ቴሌ ኮሚዩኒኬሽን ለሃያ አራት ሰዓት ሜሴጅ በነፃ አድርጎልን ነበር። እግዜር ይስጥልን። ማለት ይገባል። እንዲህ ነው እንጂ የልማት አጋር መሆን! በርግጥ አንዳንዶች ለግንቦት ሃያ መልካም ምኞት እንዲገልፁ ነፃ የተደረገላቸውን አገልግሎት ከበዓሉ ጋር ተያያዥነት የሌላቸውን አልፎ ተርፎም የበዓሉን ክብር ዝቅ የሚያደርጉ ሜሴጆችን ሲላላኩ ውለዋል። ይህ ነገር ያሳሰባቸው ከእኛም በላይ ለመንግስታቸው አሳቢ የሆኑ ሰዎች «ቴሌ አሰደበን!» በማለት ሲበሳጩ ቢሰማም ቴሌ ግን ለበዓሉ ድምቀት የበኩሉን አስተዋፅዖ ለማበርከት ብሎ እንጂ ክፋት አስቦ እንዳልሆነ መረዳት

ተገቢ ነው «አመድ አፋሽ» የሚያደርግ አይጠፋምና እርሱ ምን ያድርግ:: ወደፊት ሜሴጅን ሳንሱር እያደረገ «ልማታዊ ሜሴጅን ከኪራይ ሰብሳቢ ሜሴጅ» የሚለይ ቴክኖሎጂ እስኪመጣ መቻል ነው::

ወዳጄ ደግ ደጉን ማውራት ይሻላል ብዬ ነው እንጂ ርዕሳችንን አልረሳኋትም:: «ሰኔና ሰኞ» ሊገጥሙ ነው:: የሚል ነገር ስሰማ መጀመሪያ ምንም አልመሰለኝም ነበር:: በኋላ ላይ አንድ «ሚርት ነጋሪ» የሆነ ወዳጄ (ምኑን ወዳጄ ሆነው?) ብቻ ለመንግስትህ ያሰጋልና ፀልይ ቢለኝ «ምነው ያሰባችሁት ነገር አለንዴ?» አልኩት በብስጭት ይሔው ወዳጄ «በተለያየ የዲሲፕሊን ጉድለት ባለስልጣናትን ለመግደልና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ለማውደም ሲሉ በቁጥጥር ስር የዋሉትን የግንቦት ሰባት አባላት» እየጠቀሰ «እነዚህ ሰዎች የመፈንቅለ መንግስት ሙከራቸውን ያደረጉት ከሰኔና ሰኞ በኋላ ቢሆን ኖሮ መንግስት ጉዱ ፈልቶ ነበር» አለኝ:: ሚርቱን በመቀጠልም «የዛሬ አስር አመት በአስራ ዘጠኝ ዘጠና ሰኔና ሰኞ ገጥመው የነበረ ጊዜ ምን እንደተፈጠረ ታስታውሳለህ?» ብሎ ጠየቀኝ «ምን ተፈጠሮ ነበር?» አልኩት በጉጉት እና በፍርሃት:: «ኤርትራ ነገር ጀማመረችን በዛ ጦስ ህውሃት መከፋፈል ጀመረ ከዛ...» እያለ ሲቀጥል መስማት አቆሜ እውነትም ይሔ ሰኔና ሰኞ እንዳይገጥም መፀለይ ይገባል ስል ወሰንኩኝ:: እንደውም ለጥንቃቄ ብዬ ከራሴ ካላንደር ላይ በሰኔ አንድ አኳያ ያለውን ሰኞ ሰረዝኩት:: አፈር ስሆን ወዳጄ ሰኔና ሰኞ እንዳይገጥሙ እርስዎም መላ ፈልጉ!

በመጨረሻም1:- ሰሞኑን አንድ የቤተክርስተያን አባት ለአንድ ጋዜጣ ቤተክርስቲያኒቱ ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አንፃር እንደምን ትቃኛለች ለሚለው ጥያቄ ማብራሪያ ሲሰጡ ሰንብተዋል:: «አባታችን» በኢንተርኔት ንስሃ መግባት፣ ቅዳሴ ማስቀደስ፣ ስብከት መከታተል እና ሌለችም በርካታ ጉዳዮችን ቤተስኪያን መሔድ ሳያስፈልግ መፈፀም እንደሚቻል በተገቢ ሁኔታ አብራርተውልናል:: ብርሃን ይብዛላቸውና!

ታድያ የአባታችን ማብረሪያ ተከትሎ እኔን ጨምሮ በርካቶች ስንወያይበት ሰንበተናል:: እኔ በበኩሌ ቤተስኪያን በመሔድ የሚገኙትን ጥቅማጥቅሞች በሙሉ በኢንተርኔት ማግኘት ከተቻለ እሰየው እንኳንም «ፕሮግራመር» አባት ኖረን ስል አድናቆቴን ገልጫለሁኝ:: ሆኖም ሌሎች የቤተ ክህነትን ዶግማ እና ቀኖና በሚገባ እናውቃለን የሚሉ ሰዎች «አባታችንን» በተለይ «በኢንተርኔት “online” ማስቀደስ ይቻላል» በማለታቸው በጣም ተበሳጭተዋል:: በማስቀደስ ጊዜ የሚኖሩትን እንደ ቅዳሴ ፀበል መጠጣት፣ ቁርባን መቀበል የመሳሰሉትን ስርዓቶች እንደምን ሊያደርጉት ነው? ሲሉ ከመጠየቃቸውም በላይ እኒህ ቄስ በ«ፕሮግራሚንግ» ማስተርስ ሲይዙ ነው ነገር የተበላሸው ሲሉ ወቅሰዋል:: ከወቀሳው ብዛት የተነሳ ነው መሰለኝ «አባታችን» ባለፈው ሳምንት ያልኳችሁ ውሸቴን ነው ብለዋል:: እና ሞጋቾች እንኳን ደስ ያላችሁ!

በመጨረሻም 2:- ባለፈው ሳምንት እንዳወራነው ለግንቦት ሃያ ክብረ በዓል ድምቀት የተሰቀለ አንድ ቢል ቦርድ ላይ የተለያዩ የግንቦት ሃያ ፍሬዎችን ማየታችንን ጠቅሰናል:: ከነዚህም ውስጥ አንዱ የፕሬስ ውጤቶች ናቸው:: ታድያ ፎቶግራፋቸው ያልተካተተ ጋዜጣ ባለቤቶች አዘጋጆች ሰራተኞች እና የጋዜጣው ደንበኞች «የኛ ጋዜጣ የግንቦት ሃያ ፍሬ ካልሆነ የግንቦት ስንት ፍሬ ሊሆን ነው?» ሲሉ ጠይቀዋል::

ይበሉ ወዳጄ ሰዉ ከመሬት ተነስቶ ነገር ነገር ይሸተዋል ለዚህም ነው በየ ሳምንቱ «አማን ያሰንብተን!» የምልዎት:: ከሰኔና ሰኞ ቁጣ እርሱ ይጠብቀን! አሜን በሉኝ ወዳጄ::

# ለተሰናባች ባለሥልጣናት ጥቅማ ጥቅም «የወሰነው» ረቂቁ ሕግ፣

## የሀብትና ዕዳን ኦዲት የሚያካትት ድንጋጌ በሌለበት አዋጭ ሕግ ይሆናል ወይ?

## Responsibility = Response (+) bility

## ኃላፊነት (መፍትሄ የመስጠት ችሎታ)

**በመርዓዊ ሜጌሶ**

ባለፈው ሳምንት፣ ዴሞክራሲ የህግ የበላይነትን ወይም የህግን አምላክነት (ከፈጣሪ አምላክ በታች ማለት ነው) ካላነገሰ አክሳሪ ዴሞክራሲ መሆኑን በመጠኑ ባስቃኘሁበት ጽሁፍ መደምደሚያ ላይ፣ የበለጠ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ካልገጠመኝ በቀር ዴሞክራሲ በቲኦክራሲ ብርሃን ካላለፈ ውጤታማ ባለመሆኑ ላይ በገባኝ መጠን አንዳንድ ነገር ለመናገር ቃል ገብቼ ነበር:: ነገር ግን፤ «ለዛሬው ያንን አቆየው እኔን አስቀድም» የሚል የተቃዋሚ ድምጽ ብቅ በማለቱ አዲሱን ነገር ለማስተናገድ ጉድ ጉድ ማለቱን መረጥኩ::

ለተሰናባች ባለሥልጣናት ጥቅማ ጥቅም ጠቀም አድርጐ የደገሰውን ይህን ህግ አሁን ጊዜው ነወይ? እርግጥስ ያስፈልጋል ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች ላይ በበኩሌ መገለጥ ስላልተቀበልኩ በዚህ ጉዳይ ብርሃን የበራላቸው ወገኖች ካሉ የህግ አወጣጡን ከማገዝ አንጻር የበኩላቸውን ቢሉ ሀገር ይጠቀማል ብዬ ልጀምር:: አንድ ህግ ረቅቆ ረቂቁ ለህግ አውጭው ፓርላማ ሲቀርብ በዚህ ረቂቅ ላይ አስተያየት ካላችሁ በጽሁፍ ወይም በስልክ አስተያየታችሁን አቅርቡ በሚል አስተያየት አቅራቢ ያገር ያለህ ተብሎ የሚጋብዝ መሆኑ የታወቀ እንደመሆኑ በተያዘው ጉዳይ በቀረበው ረቂቅ ላይ ይህ መብት ስለመፈቀዱ መረጃ ባይኖርም ዞሮ ዞሮ መጠየቁ ስለማይቀር ህግ አውጭው ይህንን ምናልባት የቸኮለ (ወይም የፈጠነ) ሀሳብም ይመለከተው ዘንድ በትህትና ልኬአለሁ:: ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ዋናው ተደራሲ ህግ አውጭው ነውና ባለበት ኃላፊነት (Responsibility) ምክንያት ይህንንም ይመለከተዋል ብዬ ተስፋ በማድረግ ነው የላክሁለት:: መልካም!

መቼም ማንም ባለሥልጣን በሥልጣን ዘመኑ ተገልጋዩን ወይም የበታቹን ስብ (ምቾት፣ እርጋታ፣ ኮንፈረንስ....) ወይ ሰይፍ (አለማረፍ፣ አለመመቸት፣ ብስጭት ሀዘን....) «ሲያበላ» ቆይቶ፤ ወይም አልፎ አልፎ ስብና ሰይፍ በመቀላቀል «ሲመግብ» ቆይቶ ሲበቃው (ሲያበቃለት) መንበሩን መልቀቁ የማይቀር ነው:: ይኼ እንግዲያው ለማስታወስ ያህል እንጅ ሁላችሁ የምታውቁት ነው::

ወደሌላው ጉዳይ ከማለፋችን በፊት ግን አንድ ባለሥልጣን ወይም አንድ መንግስት ስብ (መልካም አስተዳደር በሚል ይገለጽ ይሆን?) ብቻ ካልመገበ የሰይፍ አስተዳደር ሊኖረው እንዴት

ይቻላል? እንዴት ያለ ፍልስፍና ወይም ምን ዓይነት አመለካከት ነው? የሚል ሙግትም ይኖራል፡፡ ሀሳቡን በመጠኑ ላብራራ እሞክራለሁ፡፡

ርግጥ ነው የፖለቲካ ሳይንስ ትምህርት በተለይ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምንጊዜም የስብ አስተዳደር ብቻ ካልተረጋገጠ አስተዳደሩ እያስተዳደረ አይደለምና፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይኼንን አልቀበልም እንደሚል የታወቀ ነገር ነው፡፡ ግን ልብ አድርጉ ይኼ አንድ አመለካከት ብቻ ነው፡፡ ሌሎች አመለካከቶችም አሉ፡፡ ብዙም ያልተለመደና በተግባር ግን በዓለም የመንግስታት የአስተዳደር ታሪክ ሲደጋገም የኖረ ልዩ አመለካከት አለ፡፡ ይህም መንፈሳዊ አመለካከት ነው፡፡ /ለክፉም ለደጉም አመለካከቱን ዕወቁት ወይም አዳምጡት፡፡/

በኋላኛው አመለካከት አግባብ /ይኼንን አመለካከት ይኼ ፀሐፊ በትጋት ያቀነቅነዋል/ ማንኛ-ውም መንግሰት አንድን ሐዝብ በስብ ወይም በሰይፍ አስተዳደር ብቻ ያስተዳድራል፡፡ ለዚህ መነሻ የሆኑ በርካታ ዘለዓለማዊ መሰረቶች ሊጠቀሱ የሚቻል ሆኖ ለዛሬው ግን ይህንን መሰረት ከትንቢት ኢሣያስ ልጠቅስ ተመርቻለሁ፡፡ ነቢዩ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ700 ዓ/ዓለም (ወይም አ/ፍዳ) በዚህ የትንቢት መጽሀፍ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 19-20 እንዲህ ሱል ተናግሯል፡-

**«እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤ እንቢ ብትለ ግን ብታምፁም ሰይፍ ይበላችሁዋል፣ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሯልና፡፡»**

እንደሚታወቀው ምድር የእግዚአብሔር ነች፡፡ በምድር ያለውን ሀብት ወይም በረከት ለመብላት የባለቤቱን ሥርዓት አክብሮ መኖር ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም የባለቤቱን ሥርዓት ሲያከብሩ በረከት ወይም ስብ ይበሉ ዘንድ ተፈቅዷል፤ ሥርዓቱን ቢተላለፉና ቢያፈርሱ ደግሞ ተቃራኒውን ሰይፍ መብላት ግዴታ ነው፡፡ ሰይፉን ወይም ስቡን በማቅረብ ረገድ ከሚያገለግሉት ኃይላት መካከል ነገሥታት ወይም መንግሥታት ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ለምሣሌ ሰዶምና ገሞራን ስንመለከት እነዚህ በገሞራ መንግስት አስተዳደር ስር የነበሩ ህዝቦች በግብረሰዶም ሀጢያት አቅላቸውን ሲስቱና መላዕክትን ለመድፈር እንኳ እስኪደርሱ ድረስ ሲስቱ በእሳትና ዲን ይጋዩ ዘነድ መለኮት ጨክኖባቸዋል፡፡ እግዚአብሔር አምላክ በመለኮት እሳት አቃጥሎ አመድ እስኪሆኑ ድረስ የተዋረዱ ነበሩ - እነዚህ ህዝቦች፡፡

እስራኤላውያን የአምላካቸውን ህግ ስተው እንደገዛ ፈቀዳቸው ሲኖሩ /እንዲመለሱ ቢለምኑም አሻፈረን ስላሉ/ በአንድ ወቅት የባቢሎንን ንጉስ ናቡከደነጾርን «ባሪያዬ ናቡከደነፆር» በማለት አስነስቶ /ትንቢት ኤርምያስ ምዕራፍ 25 ቁጥር 9 ይነበባል / እሥራኤልን ለ70 ዓመታት በምርኮኝነት አፍልሶ እንዲገዛ አድርጓል፡፡ (ናቡከደነጾርም በጊዜው ፍርድ አግኝቷል፡፡)

ከነዓናውያን በዝሙትና የሴሰኝነት ሀጢያት ስለተጨማለቁ በኢያሱ አማካይነት የምቾት ኑሮአቸውን ጥለው ተሰደዋል ወዘተ፡፡ /እንደዚህ ያሉ በርካታ ታሪካዊ ምሣሌዎች መጥቀስ ይቻላል ለማለት ነው፡፡/

እነዚህን የጠቀስንበት ዋናው ምክንያት የአንድ አገር የመንፈሳዊ የሞራል ሁኔታ የሚመጣለትን አስተዳደር ይቃኘዋል ለማለት ተፈልጎ ነው፡፡

በዚህ በመለኰታዊ  አቅጣጫ ሲታይ ስብ ወይም ሰይፍ በቀለብነት ለአንድ ህዝብ የሚቀርበው የህዝቡን የመለኰታዊ የሞራል ደረጃ ተከትሎ ነው፡፡ ለአንድ ህዝብ መለኰታዊ የሞራል ደረጃ ከፍ ማለትም ሆነ መውረድ ማነው ተጠያቂው? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ግልጽ ነው፡፡ ለዚህ ተጠያቂው /በዋናነት ቢባል ይሻላል/ የሃይማኖት መሪዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች

ምሳሌ በመሆን ህዝቡን አግባብ ባለው የመለኮት ሥርዓት ሊቃኙት ሲጠበቅባቸው ከምዕመኖቻቸው ባነሰ የመንፈሳዊ ዝቅጠት ውስጥ ተገኝተው ከሆነ /ዕውነቱ ይኼ ነው እየተባለ ነው ያለው/ ለዚህ ነገር ተጠያቂዎቹ እነሱ ናቸው:: በ2ኛ ደረጃ ተጠያቂዎቹ ራሳቸው ምዕመናኑም ናቸው ማለት ይቻላል:: የመለኮትን ህግና ሥርዓት የሚያስተምራቸው ሳይኖር እንኳ በልባቸው ክፉና ደጉን የሚለዩበት ዕውቀት እያለ ያንን በመናቅ ተላልፈው ሊሆን ስለሚችል ምዕመናንም በራሳቸው ምክንያትም ተጠያቂዎች ናቸው::

> **«ሕግ የሌላቸው አህዛብ ከባህሪያቸው የህግን ትዕዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ህግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ህግ ናቸውና፤ እነርሱም ህሊናቸው ሊመሰክርላቸው አሳባቸውም እርስ በእርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የህግ ሥራ ያሳያሉ:: /ሮሜ 2:14-15/**

ከዚህ መለኮታዊ ድንጋጌ ማየት እንደሚቻለው፣ በሰው ልብ የመለካምና ክፉ መለያ /በዘመናዊ አነጋገር ሶፍትዌር/ ይኸውም ህሊና የተባለ ስለተገጠመ፣ ማንም ሰው መምህሩ ሳያስተምረው እንኳ ትክክለኛና ስህተትን ይለያል:: ለምሣሌ መስረቅ የተገባ አድራጎት አለመሆኑን ለማወቅ ህግ ት/ቤት ገብቶ የተማረም ያልተማረም ሌብነት መሆኑን ያወቀው በዚህ ህሊና በተባለ የማንነት አለቃ አማካኝነት ነው:: በመሆኑም የሀይማኖት መምህሬ ስላልነገሩኝ፣ እሳቸውም ይህንኑ ሲያደርጉ ስላየሁ፣ እንደበደል ሊቆጠርብኝ አይገባም ማለት አይቻልም::

ስለዚህ በሀይማኖት መምህራን መሰረታዊ የኃላፊነት አለማወቅና በራሱም በምዕመኑ ለሞራል አልገዛ ባይነት ምክንያት ሰይፍ ሊያገኝን እንደሚችል ማየት ይቻላል:: ስለሆነም እንደመለኮታዊ ዕውነት ከሆነ የሞራል መበላሸት ውስጥ ተቀምጠን ከሆነ ስብ ልንበላ አንችልም:: ረግረግ ወባን እንዲያፈራ፣ የሞራል መውደቅም ሰይፍ ሊያፈራ ይተላል ነው የመለኮታዊው ሥርዓት አንድምታ::

ይህንን በዚሁ እናቁምና ብዙ ወደራቅንበት ርዕስ እንመለስለት::

ከላይ በተገለፀው አግባብ ባለሥልጣናቱ ስብ ወይም ሰይፍ አበሉንና ሥራቸውን ለቀቁ፤ ወይንም እንዲለቁ ተደረገ እንበል:: በረቂቁ ህግ «በክብር» የተሰናበቱ ወይም የለቀቁ የሚል ቅጽል ተገልጿል መሰለኝ ለጥቅማ ጥቅም ከሚያበቁ የረቂቁ መለኪያዎች ላይ ከተቀመጡ ነገሮች አንዱ በክብር መሰናበት ሳይሆን አልቀረም::

እንደሚታወቀው ባለሥልጣኑ ሥልጣን የተረከበው በሥልጣኑ ዘመን ህዝቡን በአግባቡ ለማገልገል ሲሆን እሱ ግን በሥልጣን ዘመኑ ሆን ብሎ፣ በስህተት ወይም በግዴለሽነተ ከገቢው በላይ ኃብት ይዟል እንበል:: ለምሣሌ ደመወዙ 3000 /ሶስት ሺህ ብር/ ሆኖ /በዚህ ደመወዝ ወር መዳረሱ አጠያያቂ ነው/ የ3 ሚሊዩን ብር ቤት አለው እንበል :: /ሌላ ሌላውን ለመዘርዘር ጊዜ እንደሌለን ታሳቢ ይደረግ/:: ይኼ ቤት አሁን የማነው የሚሆን?

በሰለጠኑ ዴሞክራሲያዊ አገራት የሀብት መቆጣጠሪያ ህጐች ስላሉ በተለይ በዩናይትድ ስቴትስ ማንም ባለሥልጣንም ሆነ ግለሰብ ከገቢው በላይ ሀብት ካለው የሀብት ኦዲተር ሀብቱን ወደባለቤቱ መንግሥት ተመላሽ ከማስደረግ ሌላ፣ ያንን ሰው በተከሳሽነትም ይይዘዋል:: ታዲያ በእኛስ ጉዳይ በረቂቁ ህግ ላይ ተሰናባች ባለሥልጣን በክብር ተሰናበቱ ሲባል ከደመወዝ በላይ የተገኘበት አንዳችም ሀብት ከሌለ በሚል ጭምር መሆን የለበትም ወይ?

በበኩሌ አንድ መንግሥት ለስብ ወይም የሰይፍ አስተዳደር ዘመን ቢኖረው የማይደንቀኝ ሲሆን /በበኩሌ የማምንበት ከፍ ሲል የገለጽኩት ምክንያት አለና/ ባለሥልጣኑ ከገቢው በላይ ሀብት ከተገኘ-በት ግን ያንን ማለፍ አግባብ ሆኖ አላገኘውም:: ኦዲቲንግ ባያስፈልግ በሚል ቀን ከለሊት ተግቼ የምደገፍበት የመርሆ  መሰረት አላገኘሁም:: ስለዚህ ያገሬ ፓርላማ በረቂቁ ህግ ላይ አስተያየት አምጡ ካለ ረቂቁ ህግ የሀብት ኦዲት ከተሰራ በኋላ የሚተገበርበት ድንጋጌ እንዲኖረው ካልተደረገ የተሟላ ህግ ወጥቷል ማለት አይችልም ባይ ነኝ::

ሌላው እግረመንገዴን የምጠቁመው የጥቅማጥቅሙን የመግነን ጉዳይ ነው:: ለምሳሌ የኦዲት ውጤቱ ባለሥልጣኑ የራሱ ቤት ሊኖረው እንደሚችል ቢያረጋግጥ ያ ባለሥልጣን በራሱ ቤት መኖር አይበቃውም ወይ? «ከአባ ቁፍር እሸት ተበልቶለት» እንዲለ ኢትዮጵያ አገራችን ከዚችው አንዲት ጓሮ ከምታክል ቁፋሮ ይኼን ያህል እሸት ከተበላለት አገሪቱ ምንድነው የሚቀራት? አገሪቱ ወደፊት ሲመቻት እያየን የምንጨምር ሆኖ ለጊዜው ባለሥልጣናቱ ይሁን ከኮንዶሚኒየምም ላቀ ያለ ቤት ቢሰጣቸውስ አይበቃም ወይ? ለምን ምሣሌ አይሆኑንም? ልጆቻቸውን ሰርቪስ ቤት አስተኝተው ባለ 2 መኝታስ ቢበቃቸው ምናለ? ወዘተ::

ለመሆኑ ሥልጣን በክብር ሲለቀቅ ይኼን ያኽል ሽልማት የተሰጠበት ሞዴል ድሃ አገርስ በዓለም አለ ወይ? ወይንስ እኛ  ይኼንን ሞዴል ህግ ልናደርገው ነው?

ለማንኛወም ቅርስአችን (Legacy) ታይቶ አኩሪና ሞዴል አስተዳደራዊ ቅርስ ካለን ሥልጣን ከምንለቅ ብንቀጥልስ አይሻልም ወይ? ብለን አማራጭ እናቀርብ ዘንድ ይፈቀድልን! 50 እና 60 ዓመት እኮ መብሰያ ዕድሜ እንጅ በአዕምሮ መሸምገያ ዕድሜ አይደለም:: እና ለምንድነው ለመጦር የምትቸኩሉብን ለማለትም ነው:: ደግሞስ እንዲህ ያለውን ሕግ በራሱ በፓርላማ አነሣሽነት ብናወጣው አይሻልም ወይ?

# የአስመራ ትዝታዬ

**በግርማ ካሳ**
**ከቺካጎ**

የኢትዮጵያ ሪቪው ዋና አዘጋጅ የሆኑት አቶ ኤሊያስ ክፍሌ በድህረ ገጻቸው ላይ አሥመራ ሆነው የተነሱትን ፎቶግራፎች በቅርቡ ተመለከትኩኝ:: ፎቶግራፉን ስመለከት የአስመራ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ የነበሩኩኝ ጊዜ በዚያ ያሳለፍኩትን አመታት አስታወሰኝ::

ብዙ ጊዜ በፖስት ካርድ ላይ የምናየው ፣ ዘንባባዎች በዳርና በዳር ያለበት መንገድ የሚያልፈው፣ ፒያሳ ወይንም ኮምሽታቶ በሚባለው ሰፈር ነው:: ያኔ በዚያ መንገድ ብዙ ኬክ ቤቶችና ቡና ቤቶች ነበሩ:: ትዝ ይለኛል በአምሳ ሳንቲም አንድ ኬክና ምን የመሰለ ካፑቺኖ እናገዝ ነበር:: በተለይም ሲመሽ ከመብራቶቿ ጋር ከተማዋ በጣም ታምራለች::

ከከተማው ውበት ባሻገር የማልረሳውና በውስጤ የተተከለ አንድ ሌላ ነገር ቢኖር የሕዝቡ ፈሪሃ እንግአብሔርነትና ደግነት ነበር።

እስቲ አንዳንድ ያጋጠሙኝን ላጫውታችሁ። አንድ ቀን በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ወዳለው ካፍቴሪያ እራቴን ለመብላት እየሄድኩ ሳለ ጓደኞቼ አገኙኝና «አትሄድም እንዴ?» አሉኝ። «የት?» አልኳቸው። «ንግደት» አሉኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር ያንን ቃል የሰማሁት። ጓደኞቼ ነገሩን ያውቁ ነበርና ምን እንደሆነ በዝርዝር አስረዱኝ።

ያን ቀን በአስመራ በሰሜን ምዕራብ በኩል ቪላጆ የሚባል ሰፈር፣ የሚካኤል ይሁን የገብርዔል ቤተ ክስርቲያን አለ። (የቱ እንደሆነ አሁንም አላስታውስም)። ዕለቱ የዚያ ቤተ ክርስቲያን ታቦት የሚወጣበት ቀን ነበር። ታዲያ ቤተ ክርስቲያኗ አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎች ታቦቱ በነገሰበት ቀን ግብዣ አድርገው በአካባቢው ያሉትን ሁሉ ይጋብዙ ነበር። ይሄ ስርዓት ነው እንግዲህ ንግደት የሚባለው።

ያኔ መኪና የለንም። በእግራችን ከአንድ ሰላሳ ደቂቃ በኋላ በቪላጆ ደረስን። አራት ተማሪዎች ነበርን። በሰፈሩ ስንሽከረከር «ኑ ግቡ» ብሎ የሚጠራን ሰው አጣን። ለካ ኑሮ በጣም ስለተወደደ እንደድሮ በየመንገዱ እየቆሙ «ብሉልን ጠጡልን» ማለት ቆሟል። «መቼም የዩኒቨርሲቲ ካፍቴሪያ ምግባችንን ትተን ባዶ ሆዳችንን አንመለስም» ብለን ወደ አንዱ ቤት አመራንና አንኳኳን። «እንኳን አደረሳቹሀ?» ስንል፣ አንዲት ያኔ ወደ አርባ አመት የሚጠጋት እናት፣ በእጇ ህፃን ልጅ ታቅፋ ወጣችና «ግቡ ግቡ» አለችኝ በፈገግታ። የቤቱ በር ጠባብ ነበር። ጎንበስ ብለን ገባን። የነበረችዋን ጠረጴዛ ከበብናት። በትልቅ ትሪ እንጀራ ቀረበልን። ከዚያ ሴትየዋ ድስቱን አመጣችና ወጡን እንዳለ እንጀራው ላይ ደፋችው። ብዙ ጊዜም አልፈጀብንም ትሪውን ጠረግነው። ከዝያም በትላልቅ ጣሳዎች ጠላ አመጣች፣ ምን ልበላቹሀ ምን የመሰለ መስተንግዶ ተደረገልን።

አስመራን ሳስብ፣ የአስመራ ነዋሪዎችን ሳስብ ያቺንም ሴት አብሬ አስባለሁ። ለእግዚአበሔር ፍቅር ስትል፣ እንግዳን በደስታ የምትቀበል! ችግረኛ ናት፣ ነገር ግን ከፊቷ ውስጣዊ ሰላም አላትና ሰውን የምትወድ ትልቅ ሴት ነበረች!! ያኔ በትግሪኛ አይደለም ያናገርናት። «የኔ ዘር ናቸው» ብላ አልነበረም ያስተናገደችን። ነገር ግን ትልቅ ሴት በመሆኗ እንጂ።

የማያልፍ ነገር የለምና የዩኒቨርሲቲ ትምህርታችን አጠናቀን የምረቃችን ቀን ደረሰ። ባጽዕ (ምጽዋ) በሕዝባዊ ግንባር ሐርነት ኤርትራ ሥር ከወደቀች በኋላ በምጽዋና በአስመራ መሃከል ከሚገኝ አንድ የከፍታ ቦታ፣ «ግራር» እንለው የነበረ ከሩቅ የሚተኮስ መድፍ በየጊዜው አስመራ ከተማ ላይ ያርፍ ነበር። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ አስመራ መብረሩን አቁሞ ነበር። (የጦር አይሮፕላን ግን ማረፋን አላቆመም)

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስለማይበርም ቤተሰቦቻችን ለምረቃችን ከአዲስ አበባ ሊመጡ አልቻሉም። ስለዚህ የምረቃ ስነ ሥርዓታችንን ብዙ አልጓጓንለትም ነበር።

የምረቃችን ስነ - ስርዓት ቀን በወንዶች ሽንት ቤት ውስጥ ትልቅ ፈንጂ ፈነዳ። ያን ሰዓት ለጥቂት ደቂቃዎች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ትልቅ ድንጋጤ ተፈጠረ። ወዲያው «ሻዕቢያ የደስታ መግለጫ መልዕክት ማስተላለፉ ነው» ብለን ቀልደን አለፍን። ከሩቅ በሚተኮስ መድፍ በግራር ተምሮ በፈንጂ መመረቅ ይሉታል ይሄ ነው።

ያ ቀን ከፈንጂ ፍንዳታው ሌላ የማልረሳው፣ በጣም ልቤን የነካና ከኤርትራ ሕዝብ ጋር ዘላቂ ፍቅር እንዲኖረኝ ያደረገ አስደናቂ ነገር ተፈጠረ። ቤተሰቦቼ ከአዲስ አበባ ስላልመጡ የምረቃ ልብሴን አውልቄ ወደ ዶርሚተሪ ለማምራት እየተዘጋጀሁ ሳለ ድንገት፣ አንዲት ሴትዮ አበባ ይዘው ብቅ አሉ። እትዬ ዘይዳ ነበሩ። ትንሽ እንደቆየሁ ደግሞ አንዲት አሮጊት ሴትዮ ሌላ እቅፍ አበባ ይዘው መጡ። አደይ ጸሃይቱ ነበሩ። ሁለቱም አይተዋወቁም። በአራት አመት የአስመራ ቆይታዬ የተወዳጀኋቸው እናቶች ናቸው። ያኔ ብቻዬን የሆንኩኝ መስሎኝ ነበር። ግን ከአንድም ሁለት እናቶች እንደ እናቴ ሆነው አበባ ይዘው በምረቃዬ ተገኙ።

እነዚህ ሁለት እናቶች ዶሮ አርደው ቤታቸው ድግስ አዘጋጅተው ነበር። ሁለቱም ወደ ቤታቸው እንድመጣ ፈለጉ። ግራ ገባኝ። በኋላ አንዳቸው ጋር ምሳ ሰዓት፤ሌላኛዋ ጋር ደግሞ ሲመሽ ሂጄ ከጓደኞቼ ጋር የተዘጋጀልኝን ድግስ ተካፈልኩ።

አስመራን ሳስብ፣ የአስመራን ሕዝብ ሳስብ ትዬ ዘይዳና አደይ ጸሃይቱን አስባለሁ። እነዚህ እናቶች በስጋ እናቶቼ አይደሉም። እንደነርሱ ትግሬ አይደለሁም። እንደነርሱ የኤርትራ ተወላጅም አይደለሁም። ነገር ግን የእነዚህን እናቶች የዋህነት፣ ፍቅርና ያላቸውን ፈሪሃ እዚአብሄር እናያለን። የእነዚህ እናቶች ደጎችና ለዘር ቦታ የማይሰጡ መሆናቸውን እያለን። እነዚህ እናቶች ባይወልዱኝም እናቶቼ ናቸው! እግዚአብሄር ባሉበት ቦታ ያክብራቸው።

የመጨረሻ አመት ተማሪ እያለን በአንድ ሃይ ስኩል፣ ለሶስት ወር ማስተማር ነበረብን። ባርካ ተብሎ በሚታወቅ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምርት ቤት ተመደብኩኝ። የተመደብኩበት ክፍል በጣም ረባሽ ክፍል እንደሆነ አንድ አስተማሪ አስጠነቀቀኝ። በጣም ፈራሁ። ነገር ግን ማስተማሩን ስጀምር የታዘብኩት ያ አስተማሪ ከነገረኝ የተቃረነ ሁኔታ እንደሆነ ነው። ተማሪዎቹ በጣም የሚያዳምጡ፣ በአክብሮት ከተያዙ ብዙ ሊሰሩ የሚችሉ ሆነው ነበር ያገኘ ኋቸው። አስተማሪያቸውም ብሆን ጓደኞቼም ሆነው ነበር የተለያየነው። ያኔ ከተማዋ ችግር ላይ ነበረች። እንደዚያም ሆኖ ግን ከፊታቸው፣ ከሁኔታቸው ያየሁት ፍቅርንና ደስታን ነበር።

አስመራን ሳስብ፣ የአስመራን ሕዝብ ሳስብ ያኔ ወርቃማ ዩኒፎርም ለብሰው የማስተምራቸውን ያዳምጡ የነበሩትን፣ ሳስረዳቸው ፊቴን ያዩ የነበሩትን የባርካ ተማሪዎችን አስታውሳለሁ።

እርግጥ ነው ብዙ የሚያሳዝኑ ነገሮች በአስመራ አይቻለሁ። እርግጥ ነው ከተማዋ ያኔ መለስተኛ ጦር ግንባር ነበረች። እርግጥ ነው በየጊዜው ሳይታሰብ በሻዕቢያ የሚተኮስ መድፍ ባልተጠበቀ ቦታ ያርፍ ስለነበረ ብዙ ሰዎች አልቀዋል። እርግጥ ነው በደርግ ወታደሮች የተሰሩ ብዙ ግፎች ነበሩ።

ነገር ግን እንደዚያም ሆኖ የሕዝቡ ፍቅር አሸንፎኝ ነው የጦር መሳሪያ በተሸከመ የጦር አይሮፕላን፣ መሳሪያ ላይ ተቀምጬ ከተማዋን የለቀኳት። አሁንም ለአስመራ ትልቅ ፍቅር አለኝ። አሁንም አስመራን ከአዲስ አበባ ቀጥሎ እንደከተማዬ ነው የማያት። አሁንም ያንን ሕዝብ እንደ ሕዝቤ ነው የማየው። አሁንም ኤርትራውያንን ከተቀረው ኢትዮጲያዊ እንደተለዩ ተደርጎ ሲታይ አያስደስተኝም።

በዚህ ምክንያት ነው የኤርትራን መገንጠል አጥብቄ የተቃወምኩት! አሁንም የምቃወመው። ለዚህ ነው ከመረብ ደቡብ ይኖሩ የነበሩ ወደ ኤርትራ፣ ከመረብ ሰሜን ይኖሩ የነበሩ ደግሞ ከኤርትራ በግፍ እንዲባረሩ መደረጉ ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ነው የምለው። ለዚህ ነው የባድመ

ጦርነት የወንድማማቾች የርስ በርስ ጦርነት እንጂ ከውጭ ኃይላት ጋር የሚደረግ ጦርነት አይደለም የምለው::

በአዲስ አበባና በአስመራ ዲሞክራቲክ መንግስት ቢኖር፣ በፍቅር በውይይት ለሁሉም በሚጠቅም መልኩ የኤርትራ ችግር ይፈታል የሚል ሙሉ እምነት አለኝ:: ኤርትራም ከኢትዮጵያ ጋር ትዋሃዳለች:: በሳባ ስቴዲየም ቺፓሊኒና ጊዮርጊስ ይጫወታሉ:: በአዲስ አበባ ስፖርት ኮሚሽን ፊት ለፊት ከአስመራ የመጡ እንደ ተስፋጋብር አይነት ብስክሌኞች የብስክሌት ጥበባቸውን ያሳዩናል::

ስለዚህ ትኩረት በኤርትራውያንና በተቀረው መሃከል ያለውን ያለፉት አሳሳኝ አስራ ሰባት አመታት የፈጠሯቸው ጠባሳዎች ላይ መሆን የለበትም::

ትኩረቱ በአዲስ አበባና በአስመራ፤ ህዝብን የሚያከበሩ፣ ለሕግ የበላይነት የሚገዙ መንግስትታት እንዲዘረጉ ማድረግ ላይ መሆን አለበት:: አቶ መለስ ዜናዊና ድርጅታቸው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳንና ቴዲ አፍሮን የመሳሰሉ እሥረኞችን በመፍታት፣ የሕዝብን ጥያቄ እንዲያከብሩ፣ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ደግሞ የቀድሞ የአስመራ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ ዲን የነበሩ ዶ/ር ክፍሉ ገብረ መስቀል፣ ፓስተር ሃይሌ ነአዝጊ፣ ፓስተር ተስፋጽዮን ሃጎስ የመሳሰሉ በእምነታቸው ምክንያት የታሰሩትን በመፍታት፣ ከግትርና ከእልህ ፖለቲካ ወጥተው ለሕዝብ ጥያቄ ቅድሚያ እንዲሰጡ ማድረጉ ላይ ትልቅ ግፊት መደረግ አለበት እላለሁኝ::

«ከአቶ ኢሳያስ ጋር መነጋገር ያስፈልጋል» የሚሉ ወገኖችን አልቃወምም:: ሻዕቢያም ሆነ ኢሕአዴግ አንድ ናቸው ብዬ አምናለሁ:: ሁለቱም በእናት አገራቸው ላይ ትልቅ ጥፋት እያደረጉ ያሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው:: (እነርሱ አይደለንም ሊሉ ይችላሉ:: ነገር ግን «ኢትዮጰያዊ መልኩን፣ ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይቀይራልን?» እንደተባለው ኢትዮጵያዊነት ፓስፖርት በመለወጥ ወይንም በመጣል የሚጠፋ አይደለም:: ኢትዮጵያዊነት የውስጥ የሆነ ማንም የፖለቲካ ስርዓት የማይለውጠው ማንነታችን ነው::)

«ኢሕአዴግን እናነጋግር» እንደምንለው ሁሉ ከሻዕበያም ጋር መነጋገሩን እደግፋለሁኝ:: በአንዳንድ ድረገጾች እንደምናነበው አስመራ በሮ መሄድ ወንጀል አይደለም:: ከኤርትራውያን ጋር መወያየት የኢትዮጵያን አንድነት መጉዳት አይደለም:: ከኤርትራ መሪዎች ጋር ውይይት የሚያደርጉትን ከመቃወም ይልቅ፣ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ እንዲኖር እንታገላለን እስካሉ ድረስ፣ በኤርትራ ያለውን አሰቃቂ የሰብዓዊ መብት ረገጣ ትልቅ ቦታ እንዲሰጡት ማሳሰቡ ይበጃል እንጂ::

ያ ካልሆነ ግን በኤርትራ ያሉ ወገኖቻችን በላያቸው ላይ የግፍ ቀንበር ተጭኖባቸው አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ለተቀረው ኢትዮጵያዊ መፍትሄ ይሆናሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው::

# የሀገራችን ችግር የሚፈታው
# በቅን ልቦና ስንነጋገር ብቻ ነው

ገረመው በላይ
ከቶሮንቶ

ሀገራችን ያለችበትን አስቸጋሪ ወቅት ሁላችንም የምናውቀው ቢሆንም ይህንን ችግር ለመፍታት የሚደረጉት ጥረቶች በተለያዩ ምክንያቶች ለውጤት አለመብቃታቸው በኔ ግምት የመቻቻልና የውይይት ችግር ይመስለኛል። ለዚህም ችግር መፍትሄው በቅንነት መነጋገር ብቻ ነው ብዬ አምናለሁ። ምናልባትም ይህ ፅሁፍ ብዙዎችን ላይስማማ ይችላል። የነፃው ፕሬስ አላማም እነዚህ ሀሳቦችን በመድረኩ በማንሸራሸር ለሀገራችን የሚበጀውን መፍትሄ በጋራ እንድንስማማበት ማድረግ ነው ብዬ እገምታለሁ።
ይህንን ጽሁፍ ስጽፍ ምናልባትም በዚህ በሀገራችን ጉዳይ በኔ ጽሁፍ ላይ እርማትና አስተያየታቸውን ከሚሰጡ የሀገሬ ልጆች ጋር ሀሳብ ለመለዋወጥና ለሀገራችን ይበጃል በምንለው ጉዳይ ላይ የመነጋገሪያ ርዕስ ይሆናል ብዬም በመገመት ነው።

ባለፉት አመታት በሀገራችን ለተከሰቱት የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ ችግሮች ተጠያቂዎቹ በተለያየ ወቅት የተነሱት ገዥዎቻችን እንደሆኑ አያጠያይቅም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የነበሩትን የቀዳማዊ ሀይለ ሥላሴ የደርግና የወቅቱን ኢህአዴግን የአገዛዝ ሥርአት ብንዳስስ ሶስቱም ተመሳሳይነት አላቸው ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም። የቀዳማዊ ሀይለ ሥላሴ ሥርአት በአንድ መልኩ የተረጋጋ ቢመስልም በዉስጡ የነበሩት አስተዳደራዊ ችግሮች ግን ዛሬ ላለንበት ሁኔታ መሰረት እንደሆነ አያጠያይቅም። በተለይም የንጉሡ ሥርዓት የህዝቡን ጥያቄ ችላ ብሎ ንጉሥ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ በሚል ይትበሀል ሀገሪቱ እድገቷ እንዲቀጭጭ ማድረጉን ሁላችንም የምንስማማበት ይመስለኛል።

በንጉሡ ሥር የነበሩት ባለሥልጣናት ከግለኝነት ጥቅም በመነጨ «ግርማዊ ሆይ» ከማለት ውጭ ሀገራችንና ህዝባችን ይህን ይፈልጋሉ የሚል ድፍረት በማጣታቸው ዛሬ ላለው ችግር መሰረት ነው ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም።

አድርባይነትና ጥቅመኝነትም የእኛ የኢትዮጵያውያን መሠረታዊ ችግር እንደሆነ ሁሉም ይረዳዋል የሚል እምነት አለኝ። መለስ ብለን ታሪክን ብንመረምር በተለያዩ ጊዜያት የለውጥ ጥያቄ ያነሱ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች በገዢው በትር እየተቀጠቀጡ በተደጋጋሚ የተደረጉ የለውጥ እንቅስቃሴዎች እንዲዳፈኑ ተደርገዋል። የተነቃነቀ ጥርስ መውለቁ የግድ ነውና በንጉሱ ዘመን የተነሱት ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከሩ በ1966 በሀገሪቱ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመጽ የንጉሱ ሥርዓትና የዘውድ አገዛዝ በሀገራችን እንዲያከትም አድርጓል።

በ1967 የሀገሪቱን በትረ ሠልጣን የጨበጠው የ120ዎቹ መኮንኖች ስብስብ የህዝቡን የትግል ውጤት በመንጠቅ ለ17 አመታት የጦርነት የረሀብና ያስተዳደር እጦት ችግር ከመቼውም በከፋ መልኩ በሀገራችን ስር እንዲሰድና ከንጉሱ አገዛዝ በከፋ መልኩ ግለኝነት፣ አድርባይነትና ጥቅመኝነት የበላይነቱን መያዛቸው ሕዝባችንም ሆነ ሀገራችን ወደተሻለ እድገት እንዳይሸጋገሩ ሆነዋል:: ከራስ ቤተሰብ እስከ ጎረቤት ብሎም በሀገር ደረጃ ከመተባበር ይልቅ እርስ በርስ በመወነጃጀል ለገዢው ሥርአት ፍራሽ በመሆን የአገዛዝ እድሜው እንዲረዝም ያ ትውልድ ከፍተኛ ስተዋጽኦ አድርጎአል:: በሀገር ጉዳይ ተነጋግሮ መሥማማትን እንደ ትልቅ ሽንፈት በመቁጠር በዛን ሰአት የነበርነው ሁሉ ወይ ዝምታን አሊያም አድርባይነትን መርጠናል:: ወንድም ሆነም ጎረቤት በታጣቂዎች ወይም በዘመኑ አጠራር አብዮት ጠባቂዎች እየተቀጠቀጠ ከአጠገባችን ሲወሰድ አይተን እንዳላየን ወይም ደግሞ መንገድ መጠቆምን ሥራዬ ብለን ይዘነው ነበር:: ይህ ሁሉ ዛሬ ለወደቅንበት ችግር መሠረት እንደሆነም ዛሬም የተገነዘብን አይመስልም:: የመጣውን ሁሉ ሆ እያልን ስናዳምቅና የመብት ጥያቄን ማንሳት እንደክህደት የምንቆጥር ብዙዎች ነበርን:: በዚህም ደርግ ሥርአት አንዱን በሌላው እያስመታ ስልጣኑን አጠናክሮ ለ17 አመታት ገዝቷል::

በ1983 የደርግ ሥርአት ወድቆ የኢህአዴግ ሠራዊት መላ ሀገሪንቷን ሲቆጣጠር ከአለፈው የባሰ ሁኔታ ይመጣል የሚል ሃሳብ በሕዝቡ መሀል አልነበረም:: ለዚህም ምክንያቱ ኢህአዴግ ሀገሪቱን ሲቆጣጠር በብዙ ሀገራት የተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴና አለም ከሁለቱ ሀያላን ሀገሮች ፍጥጫ ተላቃ ወደ አንድ ሀያል ሀገር የበላይነት የተሸጋገሩበት፤ ብሎም የዉጭ ጣልቃ ገብነት በመጠኑም ረገብ ያለበት ጊዜ በመሆኑና በደርግ ጊዜ ከነበረው የሶሻሊዝም ርዕዮተ አለም የበለጠ አፋኝ ሥርአት ይኖራል የሚል የታሪክም ሆነ የሌላ ጥናቶች መረጃዎች ለመኖራቸው በተለይም በዘመኑ የምዕራቡ አለም ለሰው ልጅ መብት መከበር የሚያደርጋቸው ጥረቶችና በቀድሞው የምሥራቁ ክፍል ማለትም የሶሻሊስት አጋር ሀገሮች ውስጥ በምዕራቡ አለም ግፊት የተጀመሩት ለውጦች እንደ እኛ ነጻነት ለተጠማና በዛሬ ለውጥ የነገን ቀን የብሩህ ተስፋ ጅማሮ አድርጎ ለሚያይ ትውልድ ተስፋ ሰጪ እንደነበር የማይዘነጋ ነው::

ኢህአዴግ የመጀመሪያውን ኮንፍረንስ አካሂዶ የሽግግር መንግስት መመስረቱን ሲያውጅ ያ ብዙ ተስፋ ተጥሎበት የነበረው የአዲስ ምዕራፍ ጅማሮ ተስፋ መምከን ጀመረ:: ለዚህም ምክንያቱ በአንድ በኩል የኢህአዴግ መንግስት በደም የተገኘን ሥልጣን በምርጫ ላለማስነጠቅ የጀመረው የማግለል ወይም በኢህአዴግ ሰዎች አባባል ሂድ አትበለው እንዲሄድ አድርገው ጨዋታና በሌላው በኩል ደግሞ ተቃዋሚው ለኢህአዴግ የብልጣ ብልጥ ጨዋታ አካሄድ ተገቢውን የፖለቲካ መልስ መስጠት ባለመቻሉና በተበታተነ ሁኔታ ላይ የነበረው የተቃዋሚው ክፍል አካሄድ ግብታዊነትና ችኩልነት ብሎም ለራስ ጥቅም መቆም፤ ከሁሉም እኔ እበልጣለሁ አመለካከት እንደ ደርጉ ሥርአት ኢህአዴግም የመጀመሪያዎቹ አመታት መንገዱ ሁሉ አልጋ ባልጋ እንዲሆንለት ምክንያት ሆኗል ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም:: የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በፓርቲያቸው ፕሮግራም ዙሪያ ራሳቸውን አጠናክረው ለለውጥ አስተዋኦ ከማድረግ ይልቅ እርስ በርሰ በመጠላለፍ ኢህአዴግ እንዲጠናከር ከማድረጋቸውም በላይ አቶ መለስ ጠንካራ ተቃዋሚ አጣን እያሉ እንዲሳለቁ አድርገዋል::

ከ1983 ዓ.ም በሁዋላ የሀገር ውስጥና ስደተኛ ፓርቲዎች፤ ታማኝና ታማኝ ያልሆኑ ተቃዋሚዎች፤ ተለጣፊ ወዘተ የተሰኙት መጠሪያ ቃላቶች በፖለቲካው መዝገበ ቃላት ውስጥ ተፈጥረዋል። ፓርቲዎችም ዲሞክራሲያዊ የሚል ቅጽል በፓርቲያቸው መጠሪያ ውስጥ ከማስገባት ውጭ ዲሞክራሲያዊ ባህልን በተግባር ለመተርጎም ብቃቱን ባለማግኘታቸው ትግሉ የኋሊት እንዲጎተት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ብል ተቃውሞ የሚደርስብኝ አይመስለኝም። በአንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ ድርጅቶች ውስጥ ዛሬ ድረስ የፓርቲው ከፍተኛ ሥልጣን በአንድ ግለሰብ እጅ ተይዞ እንደሚገኝ ይታወቃል። የገዢውን ፓርቲ በኢዲሞክራሲያዊነትና በአምባገነንነት የሚወነጅሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በራሳቸው ፓርቲ ውስጥ ያለውን ኢዲሞክራሲያዊ አሰራር ለማረምና ትግሉን አጠናክሮ በሀገሪቱ ውስጥ መሰረታዊ የፖለቲካ ለውጥ እንዲመጣ ለማድረግ ጥረት ሲያደርጉ አይታይም። ገዢውን ፓርቲ በፖለቲካ ጨዋታ በልጦ ኢዲሞክራሲያዊነቱን ለማሳየት በቅድሚያ ለዲሞክራሲ መርሆዎች ማስገዛት አስፈላጊና በህዝብም ዘንድ አመኔታን ይፈጥራል የገዚው ፓርቲንም አምባገነንነት ለማጋለጥ ይጠቅማል።

የሩቁን ወይም የመጀመሪያዎቹን 13 አመታት የኢህአዴግን የአገዛዝ ዘመን እንተወውና የቅርቡን የ1997 የምርጫ ዋዜማና ከምርጫው በሁዋላ የተከሰቱትን ሁኔታዎች ብንቃኝ ያ ለለውጥ የተነቃነቀን ህብረተሰብ ምንኛ እንዳሳዘነ አገዛዙን ደግሞ ዛሬ ለደረሰበት ማንአለብኝነት እንዳበቃ ሁላችንም ምስክሮች ነን። የነጻነት ትግል መራራና አታካች እንደሆነ ለማናችንም ግልጽና በታሪክም የተዘገበ ነው። ያለ ጠንካራ ህብረት ምንም አይነት ትግል አመርቂ ውጤት ሊያመጣ እንደማይችል ሁላችንም እንስማማለን።

እንኳን የኛ የሰው ልጆች የተለያየ ከፍተኛ እውቀት ያለን ቀርቶ በዱር የሚኖሩ አራዊት እንኳ የህብረትን አስፈላጊነት ያውቁታል። ከደካማዋ ትንሿ የወፍ ዝርያ እስከ አራዊት ንጉስ እስከሆነው የአንበሳ አኗኗር ብንመረምር ያለህብረት ህይወታቸውን ሊያቆዩ እንደማይችሉ ያውቁታል። ለዚህም ነው አባቶቻችን «ድር ቢያብር አንበሳ ያስር» የሚለውን ይትበሀል የተናገሩት።

ባለፉት አመታት በሀገራችን የተነሱትን የነጻነት ትግል እንቅስቃሴዎችን መለስ ብለን ብንመለከት የውጭ ጠላትን ለመመከት ካልሆነ በቀር የራሳችንን መብት ለማስከበር ባደረግናቸው የትግል ታሪክ ውስጥ ከመተባበር ይልቅ መለያየትን፣ ከመከባበር ይልቅ መናናቅን እንጂ እንደሀገራችን ባህል ቁጭ ብሎ ተመካክሮ ለሀገራችን የሚበጃትን የተነጋገርንበት ጊዜ የለም። ቢያንስ ቢያንስ የወዳጆቻችንን ቁጥር ማብዛት ቢያቅተን እንኳ ጠላቶቻችንን መቀነስ እንደሚጠቅም ዘንግተን፤ የትላንት ወዳጆቻችንን ዛሬ ጠላት አድርገን፤ ለትግሉ መዋል የሚገባውን ሀይል በነዚህ በጊዜያዊ ልዩነት በተፈጠሩ ጥቃቅን ችግሮች ላይ ጊዜያችንን ማባከናችን ህዝባችንንም ሆነ የኛን ትግል እየደገፉ ያሉ ወዳጆቻችን ሳይቀር እንዲያዝኑብንና በኛ ተሰፋ እንዲቆርጡ አድርገናቸዋል። ዲሞክራሲያዊ ድርጅት መሰረትን ብለን አዋጅ እያስነገርን ሥልጣኑም ሀይሉም የህዝብ እንደሆነ ችላ ብለን የእኔ ድርጅት እንዲህ ነው እያልን የትግሉ ባለቤት የሆነው ህዝብ ንብረታችን እንዲሆን እንመኛለን።

ትላንት ላይ ያወጣነውንና ጀግና ነው ያልነውን ዛሬ አዋርደን ሌላ አዲስ ጀግና ለመሰየም እንሯሯጣለን። ማንዴላ፣ ቴዎድሮስ ሌላም ሌላም ስም የሰጠናቸውንና ያበባ ጉንጉን

ያነገትንላቸውን ነገ ጨካኝ አረመኔ አምባገነን እያልን ስማቸውን ከመሬት በታች ስናውል እንገኛ ለን:: ለነገሩ እኔ እስከማውቀው አንድ ሰው ጀግና የሚባለውም ሆነ በስሙ ሀውልት የሚቆመው ያ ሰው ስራውን ከጨረሰ በኋላ ነው:: እነ አብርሀም ሊንከን፤ እነ ዊሊብራንድ፤ እነ ጄኔራል ደጎል ሌሎችም ዛሬ ስማቸው በደግ የሚነሳውም ሆነ ሀውልት የቆመላቸው ሩጫቸውን ከጨረሱ በኋላ ነው:: እኛ ግን ለመሾምና ለመሻር ቸኩለን በየጊዜው ቴዎድሮሶችን፣ ሚኒሊኮችን እና ማንዴላዎችን ስንሰይምና ሰዎቹ ትንሽ ስህተት ሲሰሩ ደግሞ መሬት አውርደን እየጣልን ወርቃማውን ጊዜ ሳንጠቀምበት አልፈናል:: ዛሬም ቢሆን ከአለፈው ስህተታችን መማር ተስኖን የትግል አዙሪት ውስጥ እንገኛለን:: ረጋ ብሎ ያለፈውን ስህተት አርሞ ግራ ቀኙን አይቶ የትግሉን አቅጣጫ ከማስተካከል ይልቅ ስም በማጥፋት አንዱ አንዱን በመወንጀል ጊዜያችንን እናባክናለን:: አሁንም ባለፈው እየተቆጨና ሌላውን እየወቀሱ ከመቆዘም ይልቅ ከስህተታችን ተምረን ያለፈውን በጥሞና መርምረን ለወደፊቱ ሀገራችን ውስጥ ሰላም የሚሰፍንበትን መንገድ መፈለግ ይገባናል:: ይህንን ለማድረግ ከራሳችንና ከባላጋሮቻችን ወይም የኛን አመለካከት ከማይጋሩት ጋር ሁሉ መታረቅ እንኳ ቢያቅተን መነጋገር መቻል ይኖርብናል:: የሰሞኑ የአዲሱ የአሜሪካ ፕሬዜዳንት ኦባማ ለኢራን ህዝብ ያደረገው ንግግርና ከኩባ ጋር ሊደረግ የታቀደው የውይይት ሀሳብ ለኛም ምሳሌ ሊሆን ይገባዋል::

ሀገራችን ኢትዮጵያ የዚህ ወይም የዚያ ቡድን የግል ሀብት ሳትሆን የሁላችንም ሀገር እንደሆነች ከልባችን ማመንም ይገባናል:: ከሁሉም ጋር በቅንነት ለመነጋገር ደግሞ ከልባችን መወሰን ያስፈልጋል:: የብልጣብልጥነት የፖለቲካ አክሮባት ሀሳባችንን ከአእምሮአችን አውጥተን ለድርጊት ዝግጁነታችንን ማሳየት መቻል ይኖርብናል:: ይህንን ደግሞ በአፋችን ብቻ ሳይሆን በተግባር ለማሳየት ከአነጋገራችን ጀምሮ ጤናማ የሆኑ ቃላቶችን በመጠቀም ኢትዮጵያዊነት መከባበር እንደሆነ ለማያውቁን ሁሉ ማሳየት ይኖርብናል:: ይውደም ይጥፋ ይገርሰስ ወዘተ የሚሉ ቃላቶችን ከመዝገበ ቃላቶቻችን ማህደር መፋቅ መጀመር መቻል አለብን:: ከላይ እንደገለፅኩት «ወዳጅ ማፍራት ባንችል እንኳ ባላንጣቻችንን መቀነስ» እንደሚያስፈልገን ማወቅ ይህንን በተግባር ለመተርጎም ፍላጎቱ ሊኖረን ይገባል:: ምናልባት በብዙዎች ዘንድ ይህ አባባል አሉታዊ ትርጉም ሊሰጠው ይችል ይሆናል:: ሀቁ ግን ይህ ነው:: ሀገራችንንም፣ ህዝባችንንም፣ብሎም ራሳችንን ነጻ የምናወጣው በፍቅር በእርቅ በሰላም ብቻ እንደሆነ፤ አሊያ ግን የዚህችን ምስኪን ሀገር መከራና፤ ያ በመከራ ያሳደገንን ወገናችንን ሰቆቃ ልንታደግ እንደማንችል መገንዘብ ያስፈልገናል:: ባለፉት ዘመናት ያሰማነው አካኪ ዘራፍ ያመጣው ውጤት እንደሌለ የተገነዘብን ይመሥለኛል:: ሁልጊዜ ከግድግዳ ጋር እየተላተምን አንድ እርምጃ ፈቀቅ ማለት እንደማንችል እርግጠኞች እንሁን::

ዛሬ የሀገሪቱን በትረ ሥልጣን ጨብጦ የሚገኘውን ስርአትም ወደ ውይይት ልናመጣው የምንችለው በበሰለ የፖለቲካ ጨዋታ ስንበልጠው ብቻ ነው:: ከምርጫ 97 ማግስት ዶክተር ብርሀኑ ነጋ እንደተናገሩት ኢህአዴግ የማይገባው የሰላም ቋንቋ ብቻ ነው የሚለው አነጋገር ለኔ ትልቅ ትርጉም አለው:: ዛሬም ይህን አባባላቸውን እጋራለሁ:: አንድ ያልገባኝ ነገር ግን ለምን ዛሬ እሳቸው ይህንን የሰላም ቋንቋ ለኢህአዴግ ለማስተማር እንደሰለቹ ነው:: በኔ እምነት ከአሁን በኋላ በሀገራችን ምንም አይነት ደም መፋሰስ የለበትም ባይ ነኝ:: ደም ለማፍሰስ የፈለጉትን ግን ስለሰላምና ስለፍቅር ማስተማር ያስፈልጋል::

አራት አስርተ አመታትን ሊያስቆጥር ትንሽ የቀረው በሀገራችን እየደረሰ ያለው የደም መፋሰስ ውጤቱ ደምን በደም መመለስ ብቻ ነው:: ይህ ታሪክ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መዘጋት ይኖርበታል:: ሁለት ትውልድን ጨርሶ ወደ ሶስተኛ ትውልድ እየተሸጋገረ ያለው ይህ የእልቂት ታሪካችን ዛሬም ሆነም ነገ ምንም አይነት የሰላም ጭላንጭል የማይታይበት፤ ለሚቀጥሉት ዘመናትም መፍትሄ የሚያመጣ አይመስልም:: ስለዚህ ወደፊትም ሀገራችን የጦርነት የረሀብ የበሽታ አውድማ ከመሆን እንድትድን የሰው ህይወት ሳንቀጥፍ ለዚች ሀገር ሰላማዊና የተረጋጋ ለውጥ የሚመጣበትን መንገድ መምረጥ ይኖርብናል:: በቅድሚያ ግን ቆም ብለን ስህተቶቻችንን መመርመር፣ከግብታዊነት መቆጠብ እና በትንሽ ውጤት መፈንደቅን ማቆም አለብን:: የፖለቲካ ድርጅቶችም የእኔ አውቅልሀለሁ ፖለቲካን ማቆም አለባቸው:: ህዝብ የድርጅታቸውን አካሄድ እንዲቆጣጠር ድርጅታቸውም የህዝብ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ፕሮግራም መቀየስ ይኖርባቸዋል:: ደጋፊውም ቢሆን ድርጅት ተከፋፍሎ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ድርጅቶች በነዚያው ግለሰቦች ሲመሰረት ይህኛው ልክ ነው ያኛው ተሳስቷል ከማለት ወይም ሌላ ምክንያት እየሰጠን ጊዜያችንን በንትርክ ከማሳለፍ ተቆጥበን የፓርቲዎቹን አላማና ፕሮግራም መመርመር ብሎም ይህንን ስልጣን እኔ አልሰጠኋችሁም ብሎ በመጠየቅ የፓርቲ መሪዎች ሀላፊነትና ተጠያቂነት እንዲሰማቸው ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ማለት ህዝባዊ ስልጣን ያለው ፓርቲ ነው እንጂ የፕሮፌሰር ወይም ዶክተር እከሌ ፓርቲ ማለት አይደለም:: አለመታደል ግን ባለፉት አመታት እንዲህ አይነቱ አጠራር የተለመደ እንደነበር ሁላችንም እናስታውሳለን::

አንድ ፓርቲ ሲመሰረት አላማው ለሀገሬና ለህዝቤ እድገትን አመጣለሁ የሚል አጀንዳን ያነገበ ነው ብዬ እገምታለሁ:: ስለዚህም የፓርቲው መሪዎች ተጠያቂነት ሊሰማቸው ይገባል:: እስከአሁን ግን አለመታደል ሆኖ ማናቸውም በስልጣን ላይ ያለውም ኢህአዴግም ሆነ ተቃዋሚዎች ተጠያቂነት ያለውን አሰራር በተግባር ሲያውሉ አልታየም::

አንድ ፓርቲ እንደ ፓርቲ እታገላለሁ ሲል ይዞ የተነሳው የ50 ወይም የ150 ወይም 1000 ብሎም 2000 ከዛም በላይ አባላቱን አጀንዳ ሳይሆን ኢትዮጵያ በምትባለው ሀገር የሚኖረውን ከ80 ሚሊዮን በላይ ህዝብ አጀንዳ እንደሆነ ይሰማኛል:: ይህ ካልሆነ ትግሉ ሁሉ ለተወሰኑ ሰዎች ስምና ዝና የተደረገ ነው ብዬ እገምታለሁ:: ወደ ኋላ መለስ ብለን የ1997ትን የምርጫ ሂደት ስንመለከት ቅንጅት ምንም እንኳን የ4 ድርጅቶች ስብስብ ቢሆንም በምርጫው ወቅት ያ 80 ሚሊዮን የሚሆነውን ህዝብ አጀንዳ ይዞ እንደተነሳ በምርጫው ቅስቀሳ ወቅት ግልጽ ነበር:: ነገር ግን ከምርጫው ማግስት በኋላ የተፈጠረው የኢህአዴግ አካሄድና ተጽህኖ ሁኔታዎችን ከቁጥጥር ውጭ ቢያደርጋቸውም በራሱ በቅንጅት ውስጥ የተፈጠረው የመከፋፈል ክስተት በፓርቲው ውስጥ የነበረውን የተጠያቂነትን አለመኖር ያሳያል:: ምንም እንኳ ገዢው ፓርቲ ያለውን ሀይል ሁሉ በመጠቀም የቅንጅትን እንቅስቃሴ ለማዳከም ቢሯሯጥም በራሱ በቅንጅት ውስጥ የነበረው ግለኝነትና የተጠያቂነት ስሜት አለመኖር ብሎም በፕሮግራሙ ውስጥ ምናልባት በጽሁፍ የተካተተው ነገር ግን በተግባር የማይተረጎመው ብቸኛው የፓርቲው የስልጣን ሀይል ህዝብ አለመሆኑ የቅንጅትን እንቅስቃሴ በፍጥነት እያዳከመው እንደመጣ አያጠያይቅም::

ለምሳሌ በዛ ወቅት ገንፍሎ የነበረው የህዝብ የትግል ስሜት በቅንጅት መሪዎች ጋዜጣዊ መግለጫ እየተሰጠበት ህዝቡ የትግሉ አካል የሆነውን ሰላማዊ ተቃዉሞ እንዳያደርግ መሰናክል ከመሆኑ ባሻገር በመሪዎቹ መሀል የተፈጠረው የግል ቅራኔ ተባብሶ በፓርቲው ውስጥ ችግርን በመፍጠሩ ለኢህአዴግ የልብ ልብ በመስጠት የቅንጅት መሪዎች ለእስር እንዲዳረጉ አድርጓቸዋል:: የቅንጅት መሪዎች ወደ እስር ቤት መግባት ትግሉ የተበታተነ መልክ እንዲይዝ መሰረት ጥሏል:: ለዚህም ዋናው ምክንያት የፓርቲው የስልጣን ሀይል ህዝብ አለመሆኑ ሲሆን ህዝቡ ኢህአዴግን በመጥላት ብቻ ለቅንጅት የሠጠው ድምጽ የድርጅቱን ባለቤትነት ለህዝቡ ስላላጎናፀፈው የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች ሲታሰሩ ትግሉ የተበታተነ መልክ እንዲይዝ ሲያደርግ በሌላ በኩል ለግል ዝናና ስም በቅንጅት ውስጥ አድብተው ሲጠባበቁ የነበሩ ራስ ወዳዶች ድርጅቱ የበለጠ እንዲዳከም አድርገዋል::

ከላይ እንደገለፅኩት ቅንጅት እንደድርጅት በፕሮግራሙ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በተግባርም የፓርቲው ብቸኛ የስልጣን አካል ህዝብ መሆኑን ቢያረጋግጥ ኖሮ ፓርቲው በጥንካሬው በቀጠለ ነበር:: እዚህ ላይ አንባቢ ምናልባት ቅንጅት በምርጫ ስራ ተጠምዶ መዋቅሩን ለማስተካከል ጊዜ አልነበረውም ሊል ይችላል:: ለዚህ መልሱ ቅንጅት ለምርጫው ሲባል በአራት ድርጅቶች ተመሰረተ እንጂ እነዛ ድርጅቶች በሀገሪቱ ውስጥ ለረጅም አመታት ትግል ሲያካሂዱ የነበረና የፓርቲውን መዋቅር ህዝባዊ ለማድረግ በቂ ጊዜ የነበራቸው ነበሩ:: ለአንድ አመት እስር ቤት የከረሙት የቅንጅት አመራሮች ከእስር ከተለቀቁ በሁዋላ የተከሰተው ያው በሀገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች በሽታ የነበረው ራስ ወዳድነትና የሀላፊነት ማጣት ስሜት ነው::

የቅንጅት አመራሮች እስር ቤት በነበሩበት ወቅት በተለይ በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መሀል የተካሄደውን የትግል እንቅስቃሴና ለትግሉ መዳከም አስተዋጽኦ ያደረጉትን ምክንያቶች እዚህ ላይ መጥቀሱ አንባቢን ማድከም ስለሚመስለኝ ልለፈውና በራሱ በቅንጅት አመራሮች ውስጥ የተፈጠረውን ሁኔታ ጠቀስ አድርጌ ለማለፍ እሞክራለሁ:: እነዚያ የተከበሩና በእድሜም ሆነ በእውቀት አንቱ የተባሉ የሀገሬ ብርቅ ልጆች ከኢህአዴግ የእስር ሰንሰለት ከወጡ በኃላ የተፈጠረው ንትርክና መከፋፈል የህዝብን አደራ መካድ እንደሆነ እቆጥረዋለሁ:: ችግር ብልሀትን ያስተምራል የሚለውን አባባል ከእስር ከወጡ በኃላ ተግባራዊ ያደርጉታል ብለን ስንጠብቅ ነገሮች ሁሉ መልካቸውን ቀይረው አንዱ ሌላውን በመወንጀል ህዝብ ትልቅ ተስፋ የጣለበት ህዝባዊ ትግል እንዲመክንና የ1997 የምርጫ ውጤት ያመጣው ታላቅ ህዝባዊ ንቅናቄ እንዲበታተን ሆኗል:: በኔ አመለካከት ይህኛው ወይም ያኛው ቡድን ትክክል ነው ብዬ ለመናገር አልደፍርም:: ድንጋይ የወረወረም መዶሻም ያቀበለም የቅንጅት ቤት እንዲፈርስ ምክንያት ሆኗል:: በአንድ በኩል የገነባነውን ህብረት እያፈረስን ሌላ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ትንንሽ ድርጅቶችን መስርቶ ኑ እንተባበር ማለት መፍትሄ ነው ብዬም አላምንም:: የሞተን ድርጅት ከመቃብር አውጥቶ እታገላለሁ ማለት ወይም የፈረሰውን ድርጅት ግርግዳና ጣራ በሌላ አዲስ ድርጅት መሰረት ላይ ማቆም ለትግሉ መፍትሄ አይሆንም:: በኔ እምነት ይህ ድርጊት የሀላፊነት ማጣት የህዝብን ማንነት መናቅና የእኔ አውቅልሀለሁ ስሜት የፈጠረው ትእቢት ነው ብዬ አስባለሁ::

ኢትዮጵያ በትግሬ፣ በአማራ፣ በኦሮሞ፣ በሱማሌ፣ በወላይታ ወዘተ ባለስልጣናት ብቻ ልትለማም ሆነ ልታድግ ብሎም ሰላሟን ልታገኝ እንደማትችል ጠንቅቀን መረዳት አለብን::

ያለንበትን ሁኔተ ሁሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለዚህች ሀገር ሰላም ሊያመጡ በሚችሉ ነገሮች ላይ ከስሜታዊነት ውጭ በሆነ ቋንቋ መነጋገር መቻል ይኖርብናል፡፡ እስከ ዛሬ መነጋገር ሳንችል ያጠፋናቸውን ጊዜያት መለስ ብለን በመመርመር ስህተቶቻችንን ለማረም ዝግጁ መሆን አለብን፡፡ ይህንን ጊዜ በቸልታና በራስ ወዳድነት ችላ ብለን ካሳለፍነው ነገ ለልጆቻችን የምናወርሳት ኢትዮጵያን ማየት የምንችል አይመስለኝም፡፡ ለዚህ ትልቅ የሀገር ጉዳይ ደግሞ መቻቻል፣ መቀራረብ፣ መነጋገርና መወያየት ትልቁ የቤት ስራችን ሊሆን ይገባዋል፡፡ መናናቅን መጠላላትን ማራቅን እኔ አውቅልሀለሁ ማለትን ስድብን ከጭንቅላታችን አውጥተን መከባበርን፣ መዋደድን፣ መስማማትን እና ለነገ ማሰብን ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ እሴቶችን ወደ ህሊናችን ማስገባት መቻል ይኖርብናል፡፡

አምላካችን ኢትዮጵያን ይጠብቃት፡፡

# ማህበራዊ ፍትህ/Social Justice

**በግዛው ለገሰ**

እኩል እደል (Equal opportunity) ሁሉንም ሕዝብ በእኩል ዓይን ማየት ላይ እና ለሕዝቦች እኩል መብቶችን መስጠት ላይ ያተኩራል፡፡ ሆኖም ሁሉንም ሰው በእኩል ዓይን ማየት የግድ ፍትሃዊነትን ይመጣል ማለት እንዳልሆነ ብዙዎች ይናገራሉ፡፡ እኩል እድል የሚያቀርቡ ድንጋጌዎች ለተገለሉ ቡድኖችና የማህበረሰብ ክፍሎች ጉልህ የሆነ እኩልነትን እንዲሰጡ ከየማህበራዊ ፍትህ መርህዎች ጋር ሊጣመሩ እንደሚገባቸውም ይነገራል፡፡ በሀል ዩንቨርሲቲ የማህበራዊ ፍትህ ኘሮፌሰር የሆኑት ጌሪ ክሬይግ «Social Justice» በተሰኘ ጽሁፋቸው ማህበራዊ ፍትህን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን ያነሷቸውን እሳቤዎች በመጠቃቀስና ሰፊ ትንታኔ በመስጠት ቀጥተኛ ትርጓሜውን ያስቀምጣሉ፡፡ ለመሆኑ ማህበራዊ ፍትህ እንደምን ያለው ፍትህ ነው?

«ማህበራዊ ፍትህ ከ1970ዎቹ ጀምሮ፣ በተለይም ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት በተጠቃሽም እራሳቸውን እንደ ማህበራዊ ዲሞክራቲክ ወይም «ሦስተኛ አማራጭ (Third way)» በፈረጁት መንግስታት መካከል በፖለቲካ ሂደቱ ዳግም ይፍለቅ እንጂ ለሺህ ዓመታቶች በተለያየ መልኩ ክርክር (ውይይት) ሲደረግበት የቆየ እሳቤ ነው፡፡» የሚሉት ፐሮፌሰር ክሬይግ እሳቤው ከተለያዩ የፖለቲካ አቋሞች የሚመነጭና በመንግስት፣ በገበያው እና በግለሰብ ሚናዎች ላይ ስፋት ካላቸው አመለካከቶች ጋር የሚተሳሰር በመሆኑ አሁንም ቢሆን አከራካሪ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ምንም እንኳን ማህበራዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስታት የማህበራዊ ፍትህ አሰራር «ባለቤቶች» እንደሆኑ ቢታወቅም በሌሎቹም (ለምሳሌ በእንግሊዝ እና በአውስትራሊያ) ተቀባይነትን አግኝቷል፣ ለምሳሌ ማህበራዊ ፍትህ የበለጠ የሚሰፍነው ለግለሰባዊነት (Individualism) ልዩ መብት በሚሰጥ አሰራር በኩል እንደሆነ መንግስታቱ ይከራከራሉ - ግለሰቦች በመንግስት እርምጃዎች ሳይታፈኑ በገበያ ቦታዎች ተፎካካሪ መሆን በሚችሉበት ጊዜ፡፡ ስለማህበራዊ ፍትህ የሚነሱ የወቅቱ አመለካከቶችም ከሌሎች የኢኮኖሚያዊ ተፎካካሪነት እና

የአካባቢ ዘላቂነት (Environmental sustainability) የፖለቲካ ግቦች ጋር ያሉትን ውጥረቶች ይፋ ማድረጋቸውን ፕሮፌሰር ክሬይግ ያስቀምጣሉ፡፡

ጆን ራውልስ የማህበራዊ ፍትህ ግንዛቤ ዘመናዊ አቀንቃኝ እንደነበር ይገለፃል፡፡ በአርስቶትል፣ ህዩም፣ ሄግል፣ ካንት እና በሌሎች የሞራል ፈላስፋዎች ትንታኔ ላይ በመመርኮዝ (ማህበራዊ) ፍትህ «ፍትሃዊነት . . . የፍትህ ዋነኛ ርዕስ መሰረታዊ የህብረተሰብ መዋቅር ነው . . . ዋና ዋናዎቹ ማህበራዊ ተቋማት መሰረታዊ መብቶችን እና ግዴታዎችን የሚያከፋፍሉበትና ከማህበራዊ ትብብር (አብሮ መስራት) በመነሳት የጥቅሞችን መከፋፈል የሚወስኑበት መንገድ . . .» እንደሆነ ያብራራል ኘ ራውልስ፡፡ ፕሮፌሰር ክሬይግ ራውልስ «ከግል ማህበራት ለግለሰቦች ሊቀርቡ በሚችሉ ጥቅሞች ላይ አላተኮረም ነበር፡፡» ይላሉ፡፡ የማህበራዊ ፍትህ እሳቤ ለግለሰብ ጥቅም ትኩረት ከሚሰጥ ህብረተሰብ ጋር ያለመጣጣሙ የራውልስ ተቃውሞ «መመዘኛዎች እና እሴቶች በግል (በግለሰብ ወይም በአንድ ተቋም ውስጥ ብቻ) ሊጉለብቱ አይችሉም፡፡» ሲል በፃፈው በዶኒሰን (1998) መስተጋባቱን ፕሮፌሰሩ ያስታውሱናል፡፡ ዶኒሰን ምን ይላል፣ «ሌሎች ላይ የምንተገብረውን እራሳችንም ላይ ልንተገብረው ይገባል፡፡»

ጆን ራውልስ ሁለት መሰረታዊ መርህዎችን አስፍሯል :-

1. እያንዳንዱ ሰው እጅግ ሰፊ መሰረታዊ የእኩል ነፃነቶች ሥርዓትና ከሌሎች ሰዎች ተመሳሳይ የነፃነቶች ሥርዓት ጋር በሚጣጣም መልኩ እኩል መብት ሊኖረው ይገባል፡፡ . . .
2. ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መበላለጦች (Inequalities) ሁለቱም (ሀ) ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለሁሉም ሰው ጥቅም አምጪ እና (ለ) ለሁሉም ሰው ክፍት ከሆኑ ደረጃዎች እና ቦታዎች ጋር የተያያዙ እንዲሆኑ ሊስተካከሉ ይገባል፡፡

ከራውልስ ሁለት መርህዎች በመነሳትም ፕሮፌሰር ክሬይግ «ስለዚህም ማህበራዊ ፍትህ ከየመበላለጥ ግንዛቤ ጋር ጠንካራ ትስስር አለው» ይላሉ፡፡ እነኚህ መርህዎች ራውልስ «ሁሉም ማህበራዊ እሴቶች - ነፃነት እና እኩል፣ ገቢ እና ሀብት፣ እንዲሁም ለራስ ቦታ የመስጠት ማህበራዊ መሰረቶች - በእኩል መከፋፈል አለባቸው፤ ከእነዚህ እሴቶች ማንኛቸውም ወይም ሁሉም በእኩል አለመከፋፈላቸው ለሁሉም ሰው ጥቅም ሲባል እስካልሆነ ድረስ፡፡» ሲል ካስቀመጠው አጠቃላይ አቋም የተቀመሩ መሆናቸውን ፕሮፌሰሩ ይናገራሉ፡፡ እንዲሁም በራውልስ አመለካከት ኢ-ፍትሃዊነት ለሁሉም ጥቅም ተብለው የማይደረጉ መበላለጦች ማለት እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ «ይህ አካሄድ እኩል እድል በማግኘት፣ እኩል ሀብት በማግኘት እና እኩል ደረጃ (status) በማግኘት መካከል ያሉትን ልዩነቶች ያሳያል፡፡» ይላሉ፡፡ ፕሮፌሰር ክሬይግ፡፡ «ለእኩልነት የሚከራከሩ አብዛኛዎቹ ፖለቲከኞች እኩል እድል በማስፈኑ ረገድ ላይ ያዘምማሉ፤ ይሁንና ግን በስተቀኝ ያሉቱ በሕጎች እና ሂደቶች እኩልነት ላይ (ማለትም የመንግስት ሚና ለሁሉም ሰው በእኩል መንገድ ነፃ የገበያ ልውውጥን ማረጋገጥ መሆኑ ላይ) ሲያተኩሩ በስተቀኝ ያሉት ደግሞ የውጤት እኩልነት ላይ ያተኩራሉ፡፡»

መበላለጦች መኖራቸው የግድ ከሆነ ፍትሃዊነታቸው የሚረጋገጠው ሁሉም ሰው የመደብ ወይም የደረጃ ልዩነት ሳይደረግ እጅግ ተፈላጊ ለሆኑት ቦታዎች መፎካከር የሚያስችለው እኩል እድል ነበረው ወይ? በሚለው መመዘኛ ብቻ እንደሆነ ራውልስ ያመለክታል:: የራውልስ የማህበራዊ ፍትህ መለኪያ «የአላዋቂነት ዓይነርግብ» ሲል የሚጠራው ሲሆን በዚህ ዓይነርግብ ምክንያት «ማንም ሰው በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ቦታ፣ የመደብ ወይ ማህበራዊ ደረጃ አያውቀውም . . . ህብረተሰባቸው ለፍትህ ሁኔታዎች ተገዢ እንደሆነ የውቃሉ::» እናም ፕሮፌሰር ክሬይግ «ሰዎች የሚንቀሳቀሱት ያለምንም የግል ጥቅም ስሜት ነው::» ይላሉ::

ማህበራዊ ፍትህ ከተከፋፋይ ፍትህ (Distributive Justice) ጋር ተለዋዋጭ እንደሆነ አድርጎ የሚወስደው ሚለር (1999) ማህበራዊ ፍትህ «በህይወት ውስጥ ያሉ ጥሩ እና መጥፎ ነገሮች በሰው ልጆች ህብረተሰብ አባላት መካከል እንዴት መከፋፈል እንደሚገባቸው» ለመወሰን የሚያስችል የፖለቲካና የፍልስፍና መመዘኛ እንደሚያቀርብ ይገልፃል:: እንደ ሚለር ከሆነ እነዚህ ነገሮች አስቀድመን የምናውቃቸው የ«መልካም ህይወት» ቁሳዊ ግብዓቶችንም ያካትታሉ - ገቢ፣ ሀብት፣ ትምህርት፣ ቤት፣ ጤና እና የመሳሰሉት:: ሚለር ከማህበራዊ ፍትህ ጋር ጠንካራ ትስስር አላቸው ያላቸውን ሦስት ቁልፍ መርህዎች ነቅሷል:: እነዚህም ተገቢ፣ **አስፈላጊ** እና **እኩልነት** ናቸው::

«ተገቢ» ወይም «desert» ከተባለው ጋር በተያያዘ ትክክለኛ ህብረተሰብ (ፍትህ የሰፈነበት ህብረተሰብ) የሚባለው «ተቋሞቹ ሕዝቡ የሚገባውን ጥቅሞች ያገኝ ዘንድ የተዋቀሩበት» ነው:: ሆኖም ይህ የሚለር መርህ በተቋማት አወቃቀር ላይ የተጣበቀና ድፍን ያለ ሊሆን አይገባም፣ ይልቁንም የ«አስፈላጊ» ወይም «need» ግንዛቤዎች ወደ ጨዋታው እንዲቀላቀሉ ይጋብዛል:: ይኸውም ሀብቶች «ይገባቸዋል» በሚል መመዘኛ ብቻ ጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም፣ «ያስፈልጋቸዋል» በሚልም እንጂ:: የ«አስፈላጊ» ግንዛቤ «በግለሰባዊ ስሜት ላይ የተመሰረተ ወይም የመልካም ህይወት አመለካከትን በያዙ በተወሰኑት ብቻ የሚወሰን አይደለም . . . ሁሉም ተሳታፊ ወገኖች በሚስማሙባቸው ሁኔታዎች መረጋገጥ የሚችል ሊሆን ይገባዋል?» ሲል ሚለር ያስቀምጣል:: ይህ የማረጋገጥ ሂደት ፖለቲካዊ ሂደት ሆኖ ነገር ግን ብዙ ወገኖች በመደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ መንገድ ጉልበት (ኃይል) በማጣታቸው ምክንያት እስካሁን ተገልለው የቆዩበት ነው:: ሚለር የእኩልነት እሳቤ ለማህበራዊ ፍትህ አስፈላጊነቱ በተፈጥሮው ተከፋፋይ መሆኑ እንደሆነ ይገልፃል፤ «የተወሰነ ዓይነት ጥቅሞች - ለምሳሌ መብቶች - በእኩል መልኩ ሊከፋፈሉ ይገባል፣ ምክንያቱም ፍትህ ይህንን ይጠይቃልና::» ማህበራዊ ፍትህን ለማስፈን «ዜጐች በእኩል ዓይን የሚታዩበት፣ የመንግስት ፖሊሲ ለእያንዳንዱ ሕዝብ የሚያስፈልገውን ለማሟላት ያነጣጠረበት፣ እንዲሁም ኢኮኖሚው ሕዝቡ የሚያገኘው ገቢ እና ከሥራ ጋር የተያያዙ ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች እያንዳንዱ ሰው ከሚገባው ጋር የተነፃፀረ በሆነ መንገድ የተቀረፀ እና የተገደበ የሆነበት የፖለቲካ ማህበረሰብ» ሊኖረን ይገባል::

ፕሮፌሰር ክሬይግ ማህበራዊ ፍትህ ከዚህ አኳያ ከዜግነት መብቶች ጋር ጥብቅ ግንኙነት እንዳለው ያነሱና በ1950 ቲ.ኤች. ማርሻል "Citizenship and social class" በተሰኘ ገለፃው ያስቀመጠው የመብቶች ምደባ ያካተተውን ያስታወሳሉ:: ማርሻል መብቶችን የሲቪል መብቶች፣ ፖለቲካዊ መብቶች፣ እና ማህበራዊ መብቶች ሲል በሦስት መድቧቸዋል:: በሲቪል መብቶች ስር የንብረት መብቶች፣ ሕጋዊ ዋስትናዎች እና ነፃነቶች፤ በፖለቲካዊ መብቶች ስር ደግሞ

የመምረጥ መብት፣ የመደራጀት መብት፣ ሕገ መንግስታዊ ተሳትፎ፤ እንዲሁም በማህበራዊ መብቶች ረገድ የትምህርት፣ የጤና እና ማህበሪዊ እንክብካቤ፣ የቤት እና የገቢ ማገገሚያ መሰረታዊ ሁኔታዎች መሟላት ሊዘረዘሩ ይችላሉ፡፡

ማህበራዊ ፍትህ ቁሳዊ ያልሆኑ የህይወት ገጽታዎችንም ይነካል፤ እነዚህ ገጽታዎችም በተለያዩ ቡድኖች እና ግለሰቦች መካከል የመከባበር እና እውቅና የመሰጣጣት ወሳኝ አመለካከቶችን ያካትታሉ፡፡ ሚለረ የማህበራዊ ፍትህ ተከፋፋይነት ምልከታ ሕዝቦች እርስበርሳቸው ሲተያዩ እንደ እኩል ከሆነበት የህብረተሰብ እሳቤ ጋር መምታታት እንደሌለበት ይገልፃል፡፡ ማህበራዊ ፍትህ «በራሱ የተከፋፋይነት እሳቤ ሳይሆን የተከፋፋይነት መጠቆሚያ (ማሳያ) አለው፡፡» ይህንን ግንዛቤ ሚለር ማህበራዊ እኩልነት (Social Equality) ሲል ይገልፀዋል፤ ይኸውም ማለት «ሕዝቦች እርስ በርሳቸውን እንዴት የሚመለከቱበትና ማህበራዊ ግንኙነታቸውን እንዴት የሚመሩበት ሁኔታ» ነው፡፡ ፕሮፌሰር ክሬይግ «ይህ የጋራ (የእርስበርስ) «እውቅና የመስጠት» ወይም «የመከባበር ግንኙነት» የማህበራዊ ፍትህ ገጽታዎች በቅርብ ዓመታቶች ጠንካራ መወያያ ሆነው ቆይተዋል» ካሉ በኋላ አይ.ኤም. ያንግ (1990) "Justice and the Politics of Difference" በተሰኘ መጽሐፏ ያሰፈረችውን እንደምሳሌነት ይጠቅሳሉ፡፡ ለያንግ ማህበራዊ ፍትህ እንደ ተከፋፋይነት ጉዳይ በየግንኙነት አግባብ (Relational Context) ሊዘረጋ የሚገባ ሲሆን፣ በተለይም «የተቋማዊ ተጽዕኖ እና ጭቆና መወገድን» ጠቅሳለች፡፡

ማህበራዊ ፍትህን በማስፈኑ ረገድ የቦታ አቀማመጥም ከባድ ተጽዕኖ እንዳለው ጆሴፍ ራውንትሪ ፋውንዴሽን በ2004 መግለፁንም ፕሮፌሰር ክሬይግ አንስተዋል፡፡ በገጠራማ አካባቢ ያሉ ሕዝቦች በከተማ ካሉት በበለጠ እኩል እድል የማግኘት አጋጣሚው ይርቃቸዋል፤ ወይም በተጐሳቆለ መንደር የሚኖሩት ሁሉም ነገር ሙሉ በሆነበት መንደር ከሚኖሩት ጋር ሲነፃፀሩ ማህበሪዊ ፍትህን እጅጉን ይሻሉ፡፡

ፕሮፌሰር ጌሪ ክሬይግ ከእነዚህ ሁሉ ምልከታዎች በመነሳት ለማህበራዊ ፍትህ ሁሉን ዳሳሽ የሆነ ትርጓሜ ሊሰጠው እንደሚችል ይገልፃሉ፡፡ በድምዳሜያቸው ላይ ያስቀመጡትን ትርጓሜ አስነብበናችሁ ጽሁፋችንን እንደመድማለን፡፡ ማህበራዊ ፍትህ «ልዩነትን እና ስብጥሮሽን (divirsity) በመቀበል ላይ መሰረት ያደረገና በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በአካባቢያዊ እና በፖለቲካ ፖሊሲዎች በኩል የሚከናወን፣ እንዲሁም (1) ፍትህ ከማስፈን፣ በእኩል ዓይን ከመታየትና እኩል ውጤት ከማግኘት፤ (2) ለህልውና እና ለእኩል ዜጋነት እውቅና ከመስጠት እና የሁሉንም በራስ መተማመን ከማበረታታት፤ (3) መሰረታዊ ፍላጐቶችን ከማሟላት፤ (4) በሀብት፣ በገብ እና በህይወት እድሎች አለመመጣጠንን ከመቀነስ፤ (5) እንዲሁም እጅግ ጥቅም የተነፈጉትን ጨምሮ ሁሉንም ከማሳተፍ ጋር በተያያዙ እሴቶች የሚገለጥ የፖለቲካ ግብዎች አተገባበር ነው፡፡» ብለዋል፡፡

## Rule OF Law NEWS

# በናይጀሪያ የሕግ የበላይነት እራሱ «ችግር» ሆኗል፡፡

የናይጀሪያ የኢኮኖሚ እና የገንዘብ ነክ ወንጀሎች ኮሚሽን (EFCC) ሊቀ-መንበር ፋሪዳ ዋዚሪ በ1999 ሕገመንግስቱ በተካተተው የሕግ የበላይነት ሥርዓት በኩል ፍትህን ማድረስ

የሀገሪቱን የፀረ-ሙስና ጦርነት እያዳከመው መሆኑን ተናግረዋል:: በሙስና ክሶች ምክንያት ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታየ ያለ ብዙ ሰዎች ፍርድ ቤቶች በጉዳዮቻቸው ላይ አፋጣኝ ፍርድ እንዳይሰጡ በጠበቆቻቸው አማካኝነት ማምለጫ መንገዶችን መጠቀማቸው እንዳሳዘናቸው የገለፁት ዋዚሪ የፍርድ ቤት ሥልጣንን ከጥያቄ ማስገባት እና ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ እንኳን አፈፃፀም እንዳይከናወን ምክንያቶችን መፍጠር ከዘዴዎቻቸው መካከል ሁለቱ እንደሆኑ አስታውቀዋል::

«የፍትህ ሥርዓቱ አዝጋሚ እና ነፋሳማ ነው:: በሕገመንግስታችን በተካተተው የሕግ የበላይነት መሰረት እስኪፈረድባቸው ድረስ እንደጥፋተኛ አይቆጠሩም:: . . . ይህንን ከፍተኛ ችግር በመደበኛ ወይም በተለመዱት ዘዴዎች ለመፍታት ማስመሰል አንችልም::» የሚሉት ዋዚሪ በዘገምተኛው የፍርድ ሂደት ምክንያት አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ጉዳዮችን የሚያዩ ዳኞች «ወይ ይሞታሉ፣ ጡረታ ይወጣሉ፣ አልያም ይዛወራሉ::» ብለዋል:: ስለዚህም ቢያንስ ንብረቶችን በማስመለሱ ረገድ የፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔን መሰረት ያላደረገ ሕግ (non-conviction-based legislation) ለናይጀሪያ አስፈላጊ እንደሆነ ሊቀ-መንበሯ «ሊኖረን የሚገባ ሕግ ነው» ሲሉ ገልፀዋል::

«ጥፋት ሰሪዎች ፍርድ ቤት ቀርበው ካልተወሰነባቸው ምንም ዓይነት የፍርድ ሥርዓት፣ የጥፋተኝነት ወሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ ሳያስፈልግ ቢያንስ ንብረታቸውን እንዲወረስ ማድረግ ይቻላል:: በማጭበርበር የተያዙ ንብረቶችን ማስመለስን የሚጠይቅ እና ሙሰኞቹ ቀድሞውንም የማይገባቸውን ንብረት መጠቀማቸውን የሚነፍግ ሕግ ነው::» ሲሉ ፋሪዳ ዋዚሪ ከተናገሩ በኋላ ይህ ሕግ በተባበሩት መንግስታት ፀረ-ሙስና ስምምነት (Convention Against Corruption) ላይም መሰረት እንዳለው ጠቁመዋል:: «ብሔራዊ ጉባዔው አፋጣኝ ትኩረት ሰጥቶት በሕግነት እንዲፀድቅ ተስፋ አደርጋለሁ» ብለዋል:: ጨምረውም በናይጀሪያ እስካሁንም መልካም አስተዳደር ኖሮ እንደማያውቅ በመጥቀስ «አሁን ያለው ዴሞክራሲ ያለ መልካም አስተዳደር ነው::» ሲሉ ተናግረዋል - የናይጀሪያ የኢኮኖሚ እና የገንዘብ ነክ ወንጀሎች ኮሚሽን ሊቀ-መንበር ፋሪዳ ዋዚሪ::

## የማይነበብ

# «ግንቦት 20 የነፃነት በዓል ነው ወይንስ የድል በዓል?»

እኔ የምለው የግንቦት ወር ስንት ቀን ነው ያለው? ረዘመብኝሳ! ምናልባት ወሩ ከመግባቱ በፊትም ሆነ ከገባ በኋላ በየሚዲያዎቹ፣ በየካፊቴሪያዎቹ፣ በየመንግስታዊ መግለጫዎቹ እና በመሳሰሉት ግንቦት ልደታ፣ ግንቦት ሰባት ፣ ግንቦት ሃያ፣ ግንቦት ሞቃቱ . . . የመሳሰሉት

እየተባለ ሲነገር መሰንበቱ ይሆን እንዲህ ወሩን ቀኑ-ብዙ ያደረገው? ለነገሩ እናንተ የማይነበበውን በትኩረት የምታነቡት አላንባቢዎቼ ትታዘቡኛላችሁ ብዬ ነው እንጂ ወሩስ እንዲህ ረዝሞ የታየኝ የኪሴ ባዶ መሆን እና የ30 ርቀት አሳስቦኝ ነው፡፡ እውነቴን ነው የምላችሁ እንደ 30 የትኛዋም ፍቅረኛዬ ናፍቃኝ አታውቅም፤ የሆነ ሰዓት ላይ እራሷ ቁጥሯ እንኳን ውልብ ትልብኛለች፡፡ ጋዜጣ እያነበብኩኝ እንኳን «ወደ ገጽ 30 ዞሯል» ሲለኝ አንዳች ነገር ልቤን 30 ቦታ ይሰነጣጥቃታል፡፡ ይሄን ያህል ደሞዝ ናፋቂ መሆኔን ለናንተ ተናግሬ እንኳን ፋታ ባገኝ ብዬ ነው፡፡

ያም ሆነ ይህ በቀኑ-ግንቦት 20 ጠዋት በታክሲ እየሄድኩኝ ነው፡፡ ሥራዬ በዓል፣ አወዳመት፣ የድል ወይም የነፃነት ቀን ስለማይል ቤቴ ተቀምጬ የኢቴቪ የግንቦት 20 ክፍል 18 ፕሮግራምን እየተመለከትኩኝ በዓሉን ለማክበር አልታደልኩም፡፡ ብቻ ታክሲ ውስጥ ነኝ፡፡ ወያላው (ረዳት ማለት ይቻል ነበር ወያላ ስለተለመደ ነው) «ለበዓሉ ድምቀት ጠጋ፣ ጠጋ እያላችሁ» እያለ ይጠቀጥቀን ጀመር፡፡ ወዲያውም ከወደኋላ «ስማ! በዓሉ እኮ የነፃነት እንጂ የመጨናነቅ አይደለም» የሚል ጉርናና እና ወደ አንድ የሀገራችን ቋንቋ የሚያመዝን ንግግር እኔም፣ ወያላውም፣ ሌሎች ተሳፋሪዎችም ጆሮዎች ውስጥ ዘልቆ ገባ፡፡ ታዲያ ያ የጥያቄ ምንጭ የሆነው ዓዕምሮዬ «በዓሉ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም እንዴ? ለምን ሌላውስ ተሳፋሪ (እኔንም ጨምሮ) እስካሁን ድረስ በበዓለ-ነፃነቱ ቀን መጨናነቅን መርጦ ጭጭ አለ?» ሲል እራሴኑ ጠየቀኝ፡፡ እኔ ግን ለዓዕምሮዬ ጥያቄ መልስ መፈለጉን ትቼ የተሳፋሪዎቹን እና የወያላውን ሁኔታ እየታዘብኩኝ ነበር፡፡ ሁሉም ለይስሙላ ያህል የለሆሳስ ፈገግታ አሳዩና በታክሲው ውስጥ ወፍራም ፀጥታ ሰፈነ፣ ወያላውም በሩን ዘግቶ ሾፌሩን «ሳበው» አለው፡፡ ለዚያ ወያላ ግንቦት 20 የነፃነት ቀን ሁኖ አለማለፉን ከፊቱ መረዳት ቻልኩኝ፡፡

የታክሲስ ነገር እኔም ምርር ብሎኛል ታክሲ አጥቶ ተደርቦ ለሚጫነው ሰው ቢዬ እንጂ (ነግ በኔ ነዋ) «ተጠጋ» ሲሉኝ «ለምን ብዬ?» በላቸው ያሰኘኛል፡፡ ሆኖም በዚያ ታክሲ እየሄድን ጥቂት እንደተጓዝን ቅድም እንደዚያ ተናግረው፣ እንደዚያ ተሳፋሪውን ሁሉ ጭጭ ያስባሉልኝ ሰው ወረዱ መሰለኝ ከጐኔ ተቀምጦ የነበረ አንድ ሌላ ሰው «ግንቦት 20 የነፃነት በዓል ነው ወይንስ የድል በዓል?» ሲል ጠየቀኝ፡፡ ይሄን ጊዜ ወያላው ከየት መጣ ሳይባል «ሁለቱም!» በማለት ሲመልስ በቅድሙ ተግባሩ መጸጸቱን ተረዳሁኝ፡፡

ከዚያማ ለሰውዬው ጥያቄ ምላሽ ይገኝ ይሆናል በማለት ሾፌሩን ሬዲዮን እንዲከፍትልን ጠየቅነው፡፡ እኔ ግን ሬዲዮኑን አልነበረም የምሰማው፡፡ የጥያቄ ምንጭ እንደነበር የማውቀው ዓዕምሮዬን እንዴት ይህንን ጥያቄ እስከዛሬ እንዳላነሳው አብጠለጥለው ጀምሬያለሁ፡፡ ከዓዕምሮዬ ጋር አንድ ሁለት ተባባልንና በኋላ ላይ መልሱን በጋራ ለማፈላለግ ተስማማን፡፡ ዓዕምሮዬም አለኝ «ከግንቦት 20 በፊት (የሰማንያ ሦስቱን ማለቱ ነው) ነፃነትም ድልም እንዳልነበረ እርግጥ ነው፡፡ ግንቦት 20 ሲመጣ (አሁንም የሰማንያ ሦስቱን ማለቱ ነው) ችግር፣ ርሃብ፣ ድርቅ ... የመሳሰሉት ድል ባይመቱም ቢያንስ ደርግ የተባለው መንግስት ድል ተመቷልና ድል ይዞ መጥቷል ብለን የድል በዓል ልንለው እንችላለን፡፡» ዓዕምሮዬን በትኩረት አንገቴን እየነቀነኩኝ እያደመጥኩት ነው፡፡ «ነገር ግን» አለኝ አዕምሮዬ ግንባሩን ቅጭም አድርጐ «ነገር ግን የነፃነት በዓል ለመሆን ግንቦት 20 ሲመጣ (ያው የሰማንያ ሦስቱን ነው) የነፃነት ዝናብንም ይዞ መጥቷል ወይ? አሁንስ ዝናቡ መዝነቡን አላቋረጠም ወይ? ብለን መጠየቅ አለብን፡፡» አለኝ፡፡

እኔም «ተረጋጋ፣ ይሄ በጥያቄና መልስ የሚታወቅ አይደለም፤ የመስክ ጥናት ይጠይቃል።» አልኩትና ነገሩን አንጠልጥለን ተውነው። (እንዲሁም የግንቦት 20 በዓልን ለማድመቅ በከተማችን በተለጣጠፉ ፖስተሮች ላይ የግንቦት 20 ፍሬዎች ተብለው የተዘረዘሩ የፕሬስ ውጤቶችን ስመለከት በአሁኑ ሰዓት ደብዛቸው የጠፉ ወደሰባት የሚጠጉ ጋዜጦችን ተመልክቼ ግር ብሎኝ ነበር። የግንቦት 20 ፍሬ እንዲህ በቀላሉ ይከስማል እንዴ? የሚለውን እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ከዓዕምሮዬ ጋር ተወያይተንባቸው በንጥልጥል አልፈናቸዋል።)

ለማንኛውም ሰሞኑን አንድ ወሬ ሰምቼ እንደማስገረምም አድርጉኛል። በሽብር ሥራ ሲንቀሳቀሱ እንደነበር ሲነገርላቸው የቆየው እና ቅርንጫፋቸውን እዚሁ እኛው አገር ከፍተው ዋና መቀመጫቸው እዚያው ከዲያስፖራው ጋር ነው የተባለላቸው ግንቦት ሰባት ተብዬዎቹ ኤርትራ ገቡ። እንዲያው ይሄንን ወሬ እንደሰማሁኝ (ቲኒሽ ቲኒሽዬ ፖለቲካ ገባኝ መሰለኝ) «የኢትዮጵያ መንግስት ጥንቁቅ ነው» አልኩኝ። ምነው እንደውም ባለፈው ሳምንት ባላነበባችሁት የማይነበበው ፅሁፌ ላይ ከኢትዮጵያ የተባረሩት ኤርትራዊያን እንዲመለሱ ተፈቀደላቸው ... ምናምን ብዬ አላጫወትኳችሁም? ያኔ ታዲያ የኢትዮጵያ መንግስት ሕዝቦቹን ለማቀራረብ ብሎ ያደረገው እንደሆነ ቢገልጽም በዓለም አቀፍ ደረጃ መልካም ገጽታን ለመገንባትም ይረዳዋል ... ምናምን እያልን ተጨዋውተን ነበር። አሁን ግን ሲገባኝ የኤርትራን መንግስት አስቀድሞ ሌጣውን ማስቀረትም ሌላው ዓላማው ሊሆን እንደሚችል ገምቻለሁ (ያው ግምት ነው)። ወላ ግንቦት ሰባት ሆነ ማንም ኤርትራ ቢገባ ትልቁ ኃይል ያለው ከሕዝብ ነው ይባል የል?!

## ሞቲቬሽን

# እንደ ህፃናቶቹ

# 'Like the Children'

ከባንቼወሰን ወልደየሱስ

**«እውነታው ልክ እንደ አንድ የተፈጥሮ አካል፣ የሰው ልጅ ለማደግ ከፍተኛ የሆነ የውስጥ ፍላጉት አለው። ልክ ዕፅዋቶች በበቂ ፀሀይና ውሃ ምንም ነገር ተቋቁመው እንደሚያድጉ ሁሉ፣ ህፃናትም ውስጣቸው የሚገኝ ነገር አስፈሪ የሆነን አውሎ ንፋስ እንዲቋቋሙ ያደረጋል። ያስ፣ ውስጣቸው የሚገኝ ትልቅ ኃይል - ትንሿ ነፋስ - ብዙ ችግሮችን ይዛ ትመጣለች።»**

**ግሎርያ ስቴነም**

ኢኮኖሚክስ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጆችም መመሪያዎች አሏቸው። ሁሉም ሰው ዕድሉ ከተሰጠው ከራሱ በላይ ትልቅ ነገር የማድረግ ፍላጐት አለው። ይህንን ፍላጐት ሁሉ ማሳካት ባይችል እንኳን፣ ራሱን ትልልቅ ስራ እየሰሩ ወዳሉ ሰዎች ውስጥ በማስገባትና በማሳተፍ የዛ ጥሩ ነገር አካል እንዲሆን ያደርጋል። ይህን ትልቅ የመሆን የሰው ልጅ ፍላጐት ዕድል ካልተሰጠው ወይም ካልፈጠርንለት ግን ፍላጐቱ ፍሬ ሳያፈራ ይቀራል።

ለምሳሌ ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለመቆም እየሞከረ ያለን ህፃን እናት ከማበረታታት ይልቅ ብትቆጣውና ብታስፈራራው ምናልባትም ለቀናቶች ወይም ለሳምንታት ያ ህፃን እንደገና ለመቆም ሙከራ አያደርግም። ምክንያቱም ምንም እንኳን ተፈጥሮ ለመቆም ሞክር፣ ጊዜህ ደርሷል እያለች ውስጥ ውስጡን ብትነግረውም ህፃኑ የትኞቹን ነገሮች ማድረግ እንዳለበት እና እንደሌለበት ስለማያውቅ ለጊዜው ዝም ይላል። የደረሰበትን ቁጣና ፍርሀት ለተወሰኑ ጊዜያት እያስታወሰ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ሙከራዎች አያደርግም። ግና ህፃን ነውና ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ፍርሀቱም ቁጣውም ይረሳል። ስለዚህ እንደገና ለመቆም ይጥራል፣ አሁንም ቁጣ ካጋጠመው ሙከራውን በድጋሚ  ያቆማል።

በእርግጠኝነት ግን ነገ ፍርሀቱን ረስቶ ተመልሶ ለመቆም ይሞክራል። ምክንያቱም መቆምና መራመድ ለህፃኑ ማድረግ የሚፈልገው እና ማንም ሊያስቆመው የማይችል ትልቅ የውስጥ ፍላጐቱ ነውና። በምትቆጣውና በምታስፈራራዋ እናት ምትክ ግን የህፃኑን ልጅ ድርጊት የምታበረታታ ብትሆን፣ ህፃኑ የበለጠ በደስታ ለመራመድ ይሞክራል። ይህም ብቻ ሳይሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ የመራመድን ስኬት ያገኛል። በእርግጥ ህፃናቶች ዛሬ ተቆጣናቸውም አስፈራራናቸውም ነገ ላይ ሲደርሱ ትላንትና ያጋጠማቸውን ሁሉ ነገር ስለሚረሱ ትላንት ሲሰሩ የነበሩትን ያን በጣም የሚፈልጉትን ማንኛውም ነገር ዛሬ ላይ ለመስራት ይሞክራሉ፣ ዛሬም ላይ በአዲስ መንፈስ፣ ኃይል እና ሞራል የሚፈልጉትን ነገር በፍቅር ይሰራሉ።

**ጊዜ ሲያልፍ ነገሮች ይለወጣሉ፤**

ችግሩ ግን ጊዜያቶች እያለፉ በሄዱ ቁጥርና ያ ህፃን ትልቅ ሰው እየሆነ ሲሄድ በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡበትን ችግሮች ልክ ህፃን ሆኖ እንዳደረገው በአዲስ ሞራልና መንፈስ ላይጋፈጣቸው ይችላል። አሁን ያ ሰው ህፃን አይደለምና እንዴት አድርጐ «እስካሁን የሰራሁት ስራ ባይታወቅልኝም እንደገና በአዱስ ሞራል የተሻለ ስራ እሰራለሁ ወይም ለሰራሁት ስራ ዛሬ ሽልማት ባላገኝም ነገን የበለጠ እሰራለሁ» ይበል? ያ ሰው በሕይወት ጉዞ ውስጥ ህፃን ሆኖ ሳለ የነበረውን ሞራልና ጥንካሬ አጥቷል። ህፃን  ሆኖ አንድ የሚወደውን ጨዋታ መጫወት ከፈለገ የሚያስቆመው ማንም ሰው አልነበረም። ምናልባት አንድ ቀን ካስቆሙት ሌላ ቀን ግን ሊያስቆሙት አይችሉም። ትልቅ የሆነው ያ ሰው ግን ዛሬ ላይ ከራሱ ሳይሆን ከሰዎች የሚጠብቅ ሆኗል። ጥሩ፣ የተሻለ እና ውስጡ ያለውን ነገር ሁሉ ለመስራት በቅድሚያ ውጫዊ የሆነው ነገር መሟላት አለበት ባይ ሆኗል። ለምሳሌ «ጥሩ ደሞዝ እንደማገኝ ሳውቅ ነው የእኔን የስራ ድርሻ የምሰራው፣ ሽልማት እንደሚሰጠኝ ካወኩ ብቻ ነው የቻልኩትን ያህል ስራ የምሰራው ወይም ምንም ነገር የምሰራው በቅድሚያ ማግኘት ያለብኝ ነገር ሲኖር ነው» ይላል። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ፣ በማስተዋልም ይሁን ባለማስተዋል ትክክለኛው የተፈጥሮ ሂደት እንደዚህ እንዳልሆነ ይኼ ሰው ረስቷል። ያ ህፃን እሱ የሚያስደስተው ነገር ላይ ብቻ ነበረ

ትኩረቱ:: ለዛም ነው ቤተሰቦቹ ምንም ይበሉት ምን ያንን ነገር ዛሬም፣ ነገም ከነገ ወዲያም ይሞክረ የነበረው:: በዚህ አካሄድ አንድ ቀን ያ ሲሞክረው የነበረ ነገር ሲሳካለት ህፃኑ ከማንም ይበልጥ ደስተኛ ይሆናል::

**ሁሉ ነገር ከእኛ ይጀምራል፣**

ይኼ ትክክለኛው አካሄድ ሆኖ ሳለ ብዙዎቻችን ግን የተገላቢጦሽ እንንቀሳቀሳለን:: በእርግጥ የሰው ልጅ በጉ ለሆኑ ማነሳሻ መንገዶች ለምሳሌ እንደ እድገት፣ ሽልማት ለመሳሰሉት ወዲያው ምላሽ ይሰጣል:: ነገር ግን እነዚህንና ሌሎች ተጨማሪ የምንፈልጋቸውን ነገሮች ለማግኘትም ይሁን ካገኘን በኋላ ለመደሰት ልክ እንደዛ ህፃን ልጅ ሁሉ ነገር ከእኛ እንደሚጀምር አንርሳ:: እኛ የምንወደውን ነገር በቅድሚያ በሙሉ አቅማችን እንስራ፣ የድርሻችንን እንስጥ:: ከዚያ ደስታን ጨምሮ የሚገባን ነገር ሁሉ ይመጣልናል::

ተፈጥሮ ሆኖ ህፃናት ትላንት ያጋጠማቸው ትንንሽ እንቅፋቶች ዛሬ ላይ ብዙ ትዝ አይላቸውም:: ለዛም ነው እነዛ ነገሮች ለሚፈልጉት ነገር መሰናክል የማይሆኑባቸው:: ደስ የሚለው ደግሞ አንድ ወይም ሁለት ህፃናት ብቻ አይደሉም እንደዚህ አይነት አካሄድ የሚሄዱት:: ሁሉም ህፃናት ናቸው እንደዚህ የሚያስቡትና የሚያደርጉት:: እስኪ ህፃናቶችን በደንብ እናስተውላቸው:: ወዲህ ወዲያ ሲሉ፣ ሲደሰቱ፣ ሲጫወቱ፣ ሲቦርቁ፣ አንድ መጫወት ወይም ማድረግ የሚፈልጉት ነገር ሲያገኙ፣ ያንን ጨዋታ በሙሉ ልባቸው ሲጫወቱ፣ ዛሬ ላይ ያንን ጨዋታ «ተዉ ይቅርባችሁ!» ቢባሉ እንኳን ዛሬን ያርፉና ነገ እንደገና ያንኑ ጨዋታ እንደገና ይጫወታሉ፣ ከዛም እነዛ በራሳቸው ንግድ የሚንቀሳቀሱት ህፃናቶች ከማንም በላይ ደስተኛ ሲሆኑ ይታያሉ:: ይህንን ደስታ ማንም አልሰጣቸውም፣ ራሳቸው ያገኙት እንጂ::

እስኪ ከእነዚህ የህፃናት ባህሪያት እኛ ምን መውሰድ እንችል ይሆን?

**«ብዙውን ጊዜ ልንጠላቸውና ልንረሳቸው በሚገቡ ትንንሽ ነገሮች ያዘንንና ያልተደሰትን እንድንሆን እንፈቅዳለን:: እኛን ጨምሮ በሌሎች ሰዎችም ጥምር ወደፊት የሚረሱ ትንንሽ ነገሮችን እያሰብን ብዙ የማይተኩ ሰዓታትን እናባክናለን:: ይኼ ይብቃንና ሕይወታችንን ትልቅ ርትጉም ላሳቸው ድርጊቶች፣ ስሜቶች፣ ሀሳቦችና ስራዎች እንስጥ::»**

**አንድሬይ ሞረስ**

## ቱሪዝም

# ኩሪፍቱ በባህር ዳር

**በናፍቆት ዮሴፍ**

ባህር ዳር ከተማ ከመልከዓ ምድራዊ አቀማመጧ ጀምሮ እስከ አየር ጠባይዋ ድረስ በደቡብ የአገራችን ክፍል ከምትገኘዋ ውቧ አዋሳ ጋር የሚያመሳስላት ነገር ይበዛል:: ለምሳሌ ዋና ዋና

አስፋልቶቿ፣ ሞቃታማነቷ፣ ዙሪያዋ በሃይቅ የተከበበ መሆኑ ከሚያመሳስሏቸው ነገሮች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ለዛሬ ባህር ዳርን በጥቂቱ አስጎበኘኋችኋለሁ፡፡ በክልሉ ምክር ቤት እና በፖሊ ቴክኒክ መሃል ላይ የሚያልፈው ማለትም ከጎንደር ወደ ባህር ዳር የሚያስገባው መንገድ ሽቅብ ሲታጠፍ ያለውን አስፋልት ቀኛችንን ተከትለን ስንወጣ ያሉትን ነገሮች እንመልከት፡፡ በቀኝ በኩል የተለያዩ ህንፃዎች አሉ፤ ከምክር ቤቱ ቀጥሎ የአማራ ልማት ማህበር (አ.ል.ማ) ሕንፃ ጣና ሐይቅን ከጀርባው ደጀን አድርጎ ተጀንኗል፡፡ አሁንም ወደላይ እየወጣን ስንሄድ በተለምዶ ማንጎ መናፈሻ የሚባለው ግቢ ይገኛል፡፡ ጊቢውን ተከትሎ ሲኬድ ጣና መሃል ላይ ጣይቱ የመዝናኛ ክበብ ይገኛል፡፡ ይህ ክበብ ጣና ሐይቁ ውስጥ የተሰራ ባርና ሬስቱራንት ሲሆን በሃይቁ ዳርቻ በርካታ የገመድ ወንበሮች ተደርድረው ሰው ተቀምጦ የሐይቁን እና የንፋሱን ትንቅንቅ እየተመለከተ የፈለገ ሻይ ቡና እያለ ያልፈለገ ዝም ብሎ ያለተዛዘ በመቀመጥ መንፈሱን ያፍታታል፡፡ ሐይቁ ውስጥ ወደተሰራው ሬስቶራንት እና ባር ለመግባት ካሜራ ለያዘም ላልያዘም ሁለት ብር መክፈል ግድ ይላል፡፡ ከባህሩ ዳርቻ እስከ ሬስቶራንቱ የሚወስደው መንገድ በብረት የተሰራ ሲሆን ዳርና ዳሩም በብረት ተከርችሟል፡፡ ምንም እንኳን ብረቱ አስተማማኝ ቢሆንም መሃል ላይ ቆሞ ጣና በቀኝ እና በግራዎ ሲያፈጥብዎ እንደማዞር ሊያደርገዎት ይችላል፡፡ በተለይ አዲስ ከሆኑ ማዕበሉ የመሻገሪያ መንገዱንም ሆነ ሬስቶራንቱን ያነቃንቀዋል፡፡ ያኔ ትንሽ ፍርሀት ቢጤ ወረር ያደርጉታል፡፡ በአጠቃላይ እዛ ለመዝናናት በግድ ኪስ ማሳበጥ አያስፈልግም፡፡ ከዚህ መናፈሻ ተመልሰን አሁንም በመጣንበት ቀጥታ በቀኝ በኩል ስንጓዝ ጊዮን ሆቴልን እናገኛለን፡፡ ይህን አንድ መስመር እንግዲህ ያስቃኘናችሁ አንድ ነገር ልንላችሁ ነው፡፡ ከጊዮን ቀጥሎ አንድ አዲስ እየተሰራ ያለ ግን ስራ የጀመረ ሎጅ አለ፡፡ ኩሪፍቱ ሎጅ ይባላል፡፡ ስንቶቻችን አዋሳ የሚገኘውን ኩሪፍቱ ሪዞርትን የመጎብኘት እድል ገጥሞን ይሆን?

ለማንኛውም ዛሬ ባህር ዳርን ውበት ካጎናጸፏት አንዱ የሆነውን ይህንን ሎጅ እናስቃኛችሁ፡፡

ከጉዮን ሆቴል ከፍ ብሎ የተሰራው ኩሪፍቱ ሎጅ ሙሉ በሙሉ ተሰርቶ የተጠናቀቀ ባይሆንም ስራ ጀምሯል፡፡ለጉብኝት ወደ ውስጥ ስንገባ ያገኘነው አልፋ ሰለሞን የተባለ ቀይ መልከመልካም ወጣት ነው፡፡ ይህ ወጣት የአዋሳ ተወላጅ ሲሆን ከአዋሳ ዩኒቨርሲቲ በሆቴል እና ቱሪዝም ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪውን ያገኘና በአዋሳ ኩሪፍቱ ሪዞርት ሲሰራ ቆይቶ ይህን ስራ ባህር ዳር ሲጀምሩ ወደ ባህር ዳር መዛወሩን አጫውቶኛል፡፡ አልፋ ሰለሞን በታላቅ ትህትና ሰላም ካለን በኋላ ወደ ጉብኝቱ ገባን፡፡ ሎጁ ከሳር ክዳኑ ጀምሮ ሃገራዊ እና ባህላዊ ሽታ ያለው ሲሆን ጉብኝት የጀመርነው ከሪሴፕሽኑ ነው፡፡ ሰራተኞች ሁሉም በንቃትና በጥንቃቄ ሰውን ለማስተናገድ ዝግጁ ናቸው፡፡ ይህ ክፍል የእንግዳ ማረፊያ ፀጉር ያለው ቆዳ የለበሱ ወንበሮች አሉት፡፡ አጠቃላይ በባህላዊ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች አምሯል፡፡ ከሪሴፕሽኑ ስንወጣ ያመራነው የስፓ አገልግሎት ወደሚሰጥበት ክፍል ነው፡፡ በዚህ ክፍል ባለሙያዎቹ በጥንቃቄ ደንበኞቻቸውን ያስተናግዳሉ፡፡ ስፓው ዘመናዊ የእግር መሰሪያ (ፔዲኪዩር) የእጅ እና የጥፍር መሰሪያ (ሜኒ ኪዩር)፣ የማሳጅ እና የመሳሰሉት አገልግሎቶች ይሰጡበታል፡፡ በዚህ ቤት ውስጥ አንድ ቀን አድረው የምግብ እና የማሳጅ እንዲሁም የፔዲኪዩር እና ሜኒኪዩር አግልግሎቶች አግኝተው 168 የአሜሪካ ዶላር ኪስዎ ውስጥ መኖሩን ማረጋገጥ ግድ ይላል፡፡

ከባህር ዳር አልፎ የአገራችን መመኪያ የሆነው ሆደ ሠፊው ጣና ሀይቅ በዛ በኩል ብቅ ሲሉ እሱም አብሮ ብቅ ይላል፡፡ ሀይቁ እና ሎጁ ርቀታቸው በጥቂት ሜትሮች የተወሠነ ነው፡፡ የመኝታ ክፍሎቹ በሣር ክዳን እና በተጠረበ ድንጋይ የተሠሩ ሲሆን በዚህ ቤት ውስጥ ዘመናዊ የሚባል ነገር አላየሁም፡፡ ሁሉም ለሀይቁ እይታ አመቺ በሆነ ሁኔታ ነው የተሠሩት፡፡ የመኝታ ክፍልዎ በረንዳ ላይ ቁጭ ብለው ጣናን እየተመለከቱ ለመዝናናት አመቺ ቢሆንም የዋጋው ነገር ትንሽ ሆድ እንደመቁረጥ ይላል፡፡ በክፍልዎ ውስጥ መጠጦች የተደረደሩበት ከእንጨት የተሠራ ሚኒ ባር አለ እራትዎን ከተመገቡ በኋላ ብላክ ሌብሉን ከፍተው አንድ ሻት ፉት ካሉ ከ168 ዶላሩ ተጨማሪ (Extra charge) ለመክፈል ይገደዳሉ፡፡ (የሙሉ ጠርሙሱን ማለት ነው) ሌላው ፕሬዚዴንሻል ፓላስ የተባለ ከሌሎቹ የመኝታ ክፍሎች ከፍ ተደርጐ የተሠራ አለ፡፡ እዚህ ክፍል ውስጥ ለማደር ሲያስቡ አሁንም ኪስዎ ዳጐስ ያለ ነገር ሊኖረው ይገባል፡፡ ለምን ቢባል የዚህ ክፍል ዋጋ 300 የአሜሪካ ዶላር ነውና ለምን ዋጋው አደገ? ይህ ፕሬዚዳንሽያል ፓላስ የተባለው ክፍል በጣም ከፍ ያለና ጣናን ምናልባትም ውቧ ባህርዳርን ከየትኛውም አቅጣጫ ጥርት አድርጐ ለማሳየት አመቺ በመሆኑና ለየት ያሉ አገልግሎቶች ሥለሚሠጡበት እንደሆነ የሩም ዲቪዥን ሠራተኛውና የእለቱ አስጐብኛችን አቶ አልፋ ሠለሞን ገልጾልናል፡፡ በአጠቃላይ ግቢው በጣም ሠፋፊ በሆኑ ባህላዊ ቁሳቁሶች የተሞላ እና ገና በጅምር ላይ ያለ ሲሆን ሲያልቅ ከዚህ የበለጠ ሊያምር እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ ሌላው ሣላነሣው የማላልፈው ገና እየተሠራ ያለውን የመዋኛ ገንዳ ነው፡፡ይህ ገንዳ ከጣና ጋር ጠርዝ ለጠርዝ ሊነካካ ምንም አይቀረውም፡፡ ለምን ከሀይቁ ጋር ተቀራረበ ስንል ጠይቀን ነበር፡፡ «ሰዎች ሲዋኙ ልክ ሀይቁ ውስጥ የዋኙ መስሎ እንዲሠማቸው ታስቦ ነው፡፡» ሲል አልፋ ያብራራል፡፡ የመዋኛ ገንዳው ደረጃው ከፍ ያለና በአገራችን ካሉት ትልልቅ ሆቴሎች መዋኛዎች ጋር የሚፎካከር ነውም ተብሏል፡፡ በነገራችን ላይ የእያንዳንዱ ክፍል ኮርኒስ በቀርከሀ የተሠራ መሆኑ ቤቱን ይበልጥ አሳምሮታል ለማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ቤት ውስጥ የውጭ ዜጐችና አባል የሆኑ ይስተናገዳሉ፡፡ ጀማሪ ቢሆንም አልጋ ሣይያዝ አድሮ አያውቅም፡፡ ከአዋሣው ኩሪፍቱ ሪዞርት የሚለየውም ቦታው መቀየሩ ብቻ ነው ሲል አልፋ ሠለሞን ለጠየቅነው ጥያቄ ሳይሠለችና ሣይሠስት መልስ ሰጥቶናል፡፡

በተረፈ ኩሪፍቱ ተሠርቶ ሲያልቅ ውቧን ባርዳርን የበለጠ ውበት ይጨምርላታል የሚል እምነት አለን፡፡ በዚህ ሁኔታ ከቀጠለች ባህርዳር በጽዳትና በፐላን የቤት አሠራር ከሀገራችን ከተሞች ቀድማ መገኘቷ የማይቀር ነው፡፡ሌላው ለባህርዳር ንጽህና ዋናውን ሚና የሚጫወተው ህዝቡ ነው፡፡ እሁድ እሁድ ሰው በነቂስ ወጥቶ አካባቢውን ያፀዳል፡፡ አስፋልት አንድ ቦታ ቢሸረፍ ወዲያው ይጠገናል፡፡ ይሄ በሁሉም የአገራችን ከተሞች ቢለመድ እላለሁ፡፡